
# ጤናችን

“የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት!”

በኢፌዴሪ ጤና ሚኒስቴር
የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት

March



ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (March 8) ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ ልዩ ዕትም
የካቲት 2011 ዓ.ም


እንኳን አደረሳችሁ !
“የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት!”
“#Balance for Better!”
በፌዴራል ጤና ሚኒስቴር
የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
በዓመት አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ የሚሰራጭ መጽሔት
43ኛው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (March 8)
የመጽሔት አጠቃላይ ዲዛይን ዝግጅት፡- በዘውዱ ጉሉማ

# ማውጫ


1. የክብርት ሚኒስትር ዴኤታ መልዕክት
2. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ተ/ ዳይሬክተር መልዕክት
3. አለም አቀፍ የሴቶች ቀን ---------------------------------------- 1
4. የሴ/ህ/ወ/ጉዳይ ዳይሬክቶሬት አበይት ክንውኖች ---------------------------------------- 2
5. ከዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ወቅታዊ ሁነቶች በጥቂቱ ---------------------------------------- 4
6. የስርዓተ-ፆታ እኩልነት አትኩሮት በተመሳሳይነት ወይስ በልዩነት? -------------------- 5
7. ድንቃ ድንቅ ---------------------------------------- 7
8. ጀግኒት - የኢትዮጵያ ሴቶች ትንሳኤ ---------------------------------------- 8
9. እንግዳችን - በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አንጋፋና ቀደምት ሴት ሰራተኞች -----------13
10. ሴቶችን በስነ ጽሁፍ ----------------------------------------17
11. ስርዐተ- ፆታ እና አካል ጉዳተኝነት ----------------------------------------18
12. ስለአልቢኒዝም ምን ያህል ያውቃሉ? ----------------------------------------19
13. ተግባራትን በፎቶ ----------------------------------------20




# የክብርት ሚኒስትር ዴኤታ መልዕክት



ወ/ሮ ሳህረላ አብዱላሂ
የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ

በቅድሚያ በአለም አቀፍ ደረጃ ለ108ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ43ኛ ጊዜ ለሚከበረው አለም አቀፍ የሴቶች ቀን እንኳን አደረሳችሁ አደረሰን፡፡ የሴቶች ጉዳይ የሰብዓዊ መብት ጉዳይ፣ የሀገር ጉዳይና የልማት ጉዳይ ነው፡፡ ሴቶችን በሁሉም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና በሌሎች መሰል ዘርፎች ውስጥ ከወንዶች እኩል ማሳተፍ ተጠቃሚና ተደራሽ ማድረግ ሀገሪቷ በአለም አቀፍ ደረጃ የተስማማችባቸው አዋጆች እንዲሁም ሀገራዊ የሆኑ በርካታ ህጎችንና ደንቦችን ተፈፃሚ ከማድረግ ባለፈ በዋናነት ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ህዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን ሴቶችንና ልጃገረዶችን ማሳተፍ ሀገሪቷ በየአመቱ ማግኘት የሚገባትን የኢኮኖሚ እድገት በእጥፍ እንድታገኝ ከማረጋገጡ በተጨማሪ ሀገራችን የተያያዘችውን ዘለቂ የልማት ግቦች ማሳካት ያስችላል፡፡

እንደ ሴክተር አለም አቀፍ የሴቶች ቀንን (March 8) ስናከብር ሁሉም የጤናው ዘርፍ ባለሙያዎች የሴቶች ፍትኃዊ ተጠቃሚነትና ተካታችነት ከማረጋገጥ አኳያ በርካታ ስራዎች መስራት እንዳለብንና እነዛን ስራዎች በቁርጠኝነት መስራትና **የሴቶችን ሁለንተናዊ ተካታችነትና ተጠቃሚነትን ካረጋገጥን እንደ ሴክተር የያዝናቸውን የትራስፎርሜሽን አጀንዳዎች እንድናሳካ በእጅጉ ያግዘናል፡፡** ለአብነትም በጤናው ሴክተር ከያዝናቸው አበይት ተግባራት የእናቶችን ሞት ለመቀነስ 9.3 ሚሊዮን ለሚሆኑ ሴቶች የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ አራተኛውን የቅድመ ወሊድ ክትትልን አስመልክቶ በስምንት ወር ዉስጥ ለ1.6 ሚሊዮን ነፍሰ ጡር እናቶች አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል፡፡ ለ1.4 ሚሊዮን ተጠቃሚዎች በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የእናቶች ማቆያ (Maternity Waiting Room) የማስፋፋት ስራ ትኩረት ተሰጥቶ 2001 ጤና ተቋማት አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛል፡፡ የድህረ ወሊድ አገልግሎትን አስመልክቶ በበጀት ዓመቱ በስምንት ወር ውስጥ 1.7 ሚሊዮን እናቶች አገልግሎት ያገኙ ሲሆን ይህም ከወሊድ በኃላ ሊከሰት የሚችለውን የእናቶችና የጨቅላ ህጻናት ህመምና ሞት ፈጥኖ ለመከላከል ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ በፌስቱላና በማህፀን መውጣት ችግር የሚሰቃዩ ሴቶችን ለመታደግም 2,436 ችግሩ ያጋጠማቸው ሴቶች ህክምና ተሰጥቷቸዋል፡፡ የጨቅላ ሕጻናት ኮርነር (NBC) በ2300 በላይ ጤና ጣቢያዎች ተቋቁሟል፡፡ የጨቅላ ህፃናት ጤና አገልግሎት የሚሰጡ ሆስፒታሎች 180 ደርሰዋል፡፡ ይህ ከብዙ በጥቂቱ ሲሆን በአጠቃላይ ግን የጤና ሚኒስቴር ሴቶች በተለያየ ዘርፍ ያልተሳተፉበትና ሴቶችን ተጠቃሚ ያላደረጉ ስራዎች ውጤት ሊኖራቸው እንደማይችል ትልቅ እምነት አለው፡፡

በመሆኑም እንደ ሴክተር ከያዝነው ግብ አንፃር የሴት ሰራተኞች በዘርፉ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በተለይ ግን የሴት አመራሮች ቁጥርና የፆታ ስብጥር በሚያበረታታና ለሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች ምሳሌ በሚሆን መልኩ በርካታ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ሴት ዳይሬክተሮችንና በታሪኩ ለየት ባለሁኔታ ሁለት ሚኒስቴር ዴኤታዎችን ወደ ኃላፊነት ማምጣት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በሴክተሩ በተደረገ ውይይትና መግባባት፤ ብቃትና አቅም ያላቸውን በክልልና በከተማ መስተዳድር ስር በሚገኙ ሆስፒታሎች ሃምሳ በመቶ (50%) የሚሆኑ ሴቶች እንዲሁም በጤና ጣቢያ መቶ በመቶ (100%) ሴቶች ኃለፊ እንዲሆኑ ውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡

በተጨማሪም በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓታችንን ሩህሩህ፣ ተገልጋይ አክባሪና ተንከባካቢ የጤና ባለሙያና የጤና አገልግሎት በመፍጠር ፍትሃዊ የሴቶች ጤና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ የበኩላችንን አስተዋፅኦ እናደርጋለን፡፡

በመሆኑም ይህንን እለት በምናስብበትና ለሴቶች ፍትሃዊ የጤናው ዘርፍ ተጠቃሚነት ስኬት ቃልኪዳናችንን በምናድስበት በዛሬው እለት መረሳት የሌለበት ነገር ቢኖር ሴቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች መስኮች ላስመዘገቧቸዉ ስኬቶች እዉቅና መስጠትና ለቀጣይ ድል ማበረታታት ተገቢ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በራሳቸው ጥረትና የተፈጠረላቸውን መልካም አጋጣሚዎች ሁሉ በመጠቀም ለውጤት የበቁ በርካታ የሃገራችንን ሴቶች ማመስገንና ሌሎችም የእነሱን ፈለግ እንዲከተሉ ማበረታታት ከምናስበው ደረጃ ሊያደርሰን ስለሚችል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በመጨረሻም እንደ ሴክተር የሴቶችን እኩል ዕድል ፍትኃዊ ተጠቃሚነትንና ተደራሽነትን ከማረጋገጥ አኳያ በሚኖረው ያላሰለሰ ጥረት እኛ የጤናው ዘርፍ ሰራተኞችና የህገራችን ህዝቦች በአጠቃላይ በትብብር መስራት ያስፈልገናል የሚል ዕምነት አለኝ ለዚህም መረጋገጥ ሁላችሁም ከጎናችን ሆናችሁ ለጋራ ዕድገት በጋራ ጥረት እንድንሰራ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

አመሰግናለሁ

**“የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት!”**

## የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ተ/ዳይሬክተር መልዕክት



ወ/ሪት ሌንሳ ዘካርያስ
የሴ/ህ/ወ/ጉ/ዳይሬክቶሬት
ተ/ዳይሬክተር

የዘንድሮው አለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሲከበር ለየት የሚያደርገው በሀገራችን በተጀመረው የለውጥ ጎዳና የሴቶች ሚና ከፍ ብሎ መታየቱ ወይም ከምንግዜውም በላይ ሴቶች በሀገሪቷ ቁልፍ የፖለቲካ ቦታ ላይ የ50 በመቶውን ድርሻ መያዛቸው ነው፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ በታሪክ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዝዳንት መሾሟ ሃገራችን እንደ ሃገር ብቻ ሳይሆን እንደ አፍሪካም ጭምር ጉልህ የሆነ የሴቶችን ተጠቃሚነትና ፍትሃዊነት የፖለቲካ ምህዳር እያሰፋች መሆኑ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ቀዳሚና ተምሳሌት መሆኗ የዘንድሮውን የሴቶች ቀን በዓልን ለየት ያደርገዋል፡፡

ሴክተራችንም ይህንን በመከተል **የወረዳ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን ለማሳካት ሴቶችን ወደ አመራርነት ማምጣት ትልቅ ድርሻ እንዳለው በማመን ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑ ሊያስመሰግነው ይገባል፡፡**
ሆኖም ግን ሴቶች ወደ አመራርነት በመጡበት ግዜ በተለያዩ ውስብስብ ችግሮች ተተብትቦ የነበረውን ብልሹ አሰራር ጋር ተላትመው ወደኋላ እንዳይመለሱ እና የአመራር ብቃታቸው ላይ ፈተና እንዳይሆን የአመራርነት ክህሎታቸውን በማሳደግ ሊገጥሟቸው የሚችሉ የስራ ላይ ተግዳሮቶችን በሳይንሳዊ መንገድ የሚፈቱበትን አቅም እንዲያጎለብቱ የሚያስችል ስልት ነድፈው እንዲንቀሳቀሱ የበላይ አመራር አካላት አጋርነት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

የሃገራችን ሴቶች ከማንኛውም ማህበረሰብ በላይ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እየተጋፈጡ የህይወትን ውጣ ውረድ ለልጆቻቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለማህበረሰባቸው ብሎም ለሃገራቸው የማይተካ ሚናቸውን ሲወጡ ቆይተዋል እየተወጡም ይገኛሉ፡፡ በዚህም በየዓመቱ የሴቶች ቀንን አስበን ስንውል በመላው ሀገሪቱ በተለያየ ምክንያት ሴት በመሆናቸው ብቻ የፆታዊ ጥቃት የሚደርስባቸውንና የደረሰባቸውን እንዲሁም በተዛባ የስርዓተ ፆታ አመለካከት ቀንበር ስር ያሉ እናቶቻችንን፤ ወጣት ልጃገረዶችንና እህቶቻችንን በማሰብ፣ በገጠሩም ሆነ በከተማው በወሊድ ምክንያት ህይወታቸውን በተለያየ ምክንያት ማለትም በጤና አገልግሎቱ መጓደል፣ ባለማወቅም ሆነ በማወቅ በስርዓተ ጾታ አድሏዊነትና መገለል ምክንያት ወደ ጤና ተቋም ሳይሄዱ ባሉበት የፆታው እኩልነት ፍትህ ሳይረጋገጥላቸው ህይወት ለመስጠት ህይወታቸው የሚያልፍ እናቶች ወደፊት እንዳይኖሩ በቁጭት ተግተን በመስራት ችግሮችን ማስወገድ ይኖርብናል፡፡

በተጨማሪም የሀገራችን ሴቶች በፀረ-ተህዋሲያን መላመድ፤ ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ እንደ ካንሰር ባሉ በሽታዎች በስፋት ወደ ጤና ተቋማት ሄደው የህክምና አገልግሎት እንዳያገኙ፣ ከወረዳ ጀምሮ የመረጃ ትስስርን እንደ ሴክተር በማጠናከር ሁሉንም የጤና አገልግሎት ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንድትጠቀም በተለይም ሴቷ የስነተዋልዶ ጤና መብቷን አውቃ ሀገሪቷ ባሏት የኢኮኖሚ አቅም ተጠቃሚ እንድትሆን ሳይንስ የደረሰበትን የጤና አገልግሎት እንድታገኝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን አጠናክሮ በማስቀጠል ሴቷ የራሷን፤ የቤተሰቧን እና የማህበረሰቧን ጤና የምትጠብቅበትንና የምታስጠብቅበትን አቅሟን እንድታጎለብት ባለንበት የስራ ዘርፍ የበኩላችንን ኃላፊነት እንድንወጣና በወጣት ሴት እህቶቻችን ላይ ስር እየሰደደ ያለው ያልተፈለገ እርግዝና መጋለጥ እያስከተለ ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ማለትም ለአባላዘርና ለኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ መጋለጥ፣ ውርጃ የሚያስከትለውን የስነ ልቦና፣ አካላዊና ጾታዊ ጥቃት ችግሮችን ከሚመለከታቸው አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በመስራት ጤናማ የነገ ሀገር ተረካቢ ሴቶች እንዲፈጠሩ ሁላችንም ኃላፊነታችንን እንወጣ በማለት ጥሪዬን ለማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

**“የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት!”**

አመሰግናለሁ፡፡

# አለም አቀፍ የሴቶች ቀን (March 8)

አዘጋጅ፦ ትሁት አየለ


የዘንድሮው አለም አቀፍ የሴቶች ቀን (ማርች 8) በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ108ኛ በሀገራችን ለ43ኛ ጊዜ የሚከበር ሲሆን መሪ ቃሉም **"የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት!"** የሚል ሲሆን ይህም የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማስቀጠል እንዲሁም ማህበራዊ ብቃትና ተሳትፎአቸውን ለማሳደግ እድሎችን የሚሰጥ ይሆናል፡፡


አለም አቀፍ የሴቶች ቀን በዓል አላማ

- በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረገውን የሴቶችን ሁለንተናዊ የትግል እንቅስቃሴ ውጤት ለመዘከር
- ሴቶች ከነበረባቸው ጭቆና ተላቀው በኢኮኖሚያዊ በማህበራዊና በፖለቲካዊ መስኮች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡
- የስርዓተ ፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ
- ሃገራችን የጀመረቻቸውን የልማት እቅዶችና ህዳሴውን ለማሳካት
- በዓለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ግንዛቤና ንቅናቄ ለመፍጠር፣
- መንግስታት የገቡትን ቃል እንዲጠብቁ ጫና ለመፍጠር፣
- በየአካባቢው የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚሰሩ ስራዎችን ለማጠናከር፣
- በሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ያሉ ልምዶችን ለመለዋወጥ፣

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ታሪካዊ አመጣጥ

እ.ኤ.አ. ከ1800 — 1900 በነበረው የግዛት መስፋፋት፣ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የኢንዱስተሪያላይዜሽን መስፋፋት ተከትሎ የተፈጠረው ያልተመቻቸ የስራ ሁኔታ፣ ዝቅተኛ ደሞዝ እና ረዥም የስራ ሰዓት በሴቶች ላይ ባስከተለው ግፍና በደል ሳቢያ፣ ፌብርዋሪ 28 ቀን 1909 እ.ኤ.አ. የሴቶች ቀን በመባል በአሜሪካ ሶሻሊስት ፓርቲ ውሳኔ በአሜሪካ መከበር ጀመረ፣ ከዚህ ውሳኔ በፊት በ1908 በሴቶች ላይ እየደረሰ ባለው ጭቆና ሳቢያ ከፍተኛ የፖለቲካ ክርክርና ሙግት ይካሄድ ነበር፣15,000 ሴቶች በኒዎርክ ጎዳና ላይ ሰልፍ በመውጣት የሥራ ሰዓት እንዲቀነስ፣ ለተሻለ ክፍያ እና የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዲከበር ድምጻቸውን አሰምተው ነበር፣ በ1910 ዓ.ም. የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የሴቶች ኮንፍረንስ ኮፐንሀገን በተደረገው የሶሻሊስት ስብሰባ ተካሄደ፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ የሶሻል-ዴሞክራቲክ ፓርቲ የሴቶች ቢሮ መሪ የሆነችው ጀርመናዊቷ ክላራ ዜትኪን የዘር፣የቀለም እና እድሜ ልዩነት ሳይኖር ሁሉም ሴቶች በየዓመቱ፣በሁሉም አገር በተመሳሳይ ቀን ድምጻቸውን እንዲያሰሙ ያቀረበችው ሃሳብ በሙሉ ድምጽ ተቀባይነት አገኘ፣ በኮፐንሀገን የተላለፈውን ውሳኔ ተከትሎ በ1911 የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 19 ተከበረ፡፡ በአሉ በተከበረ ሳምንት ባልሞላው ጊዜ ማርች 25 በኒውዮርክ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በተነሳ የእሳት ቃጠሎ 140 ሴቶች ህይወት ማለፉ ትግሉ የበለጠ እንዲጠናከር አድርጎታል፣ በመቀጠልም በተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት ውሳኔ መሰረት እ.ኤ.አ. ከ1975 ዓ.ም. ጀምሮ ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሆኖ እንዲከበር ተወሰነ፣ በዚህ የተነሳም ከ1909 ጀምሮ በየዓመቱ በተለያየ ወራትና ቀናት በበርካታ አገሮች በሰላማዊ ስልፍ እና በሌሎች የትግል መድረኮች ድምፃቸውን ማሰማት ቀጠሉ፡፡ በአጠቃላይ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 ከአውሮፓ የኢንዱስትሪ አብዮት ጋር ትልቅ ቁርኝት ያለው ነው፣ ወቅቱ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የነበራቸው ሥፍራ እጅግ ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን ኢንዱስትሪውም ሴቶችን የርካሽ ጉልበት ምንጭ አድርጎ የሚጠቀምበት ጊዜ ነበረ፣ አሰልቺ በሆነ ሥራና ደህንነታቸውን አደጋ ላይ በሚጥል የሥራ አካባቢ ምክንያት በርካታ ሴቶች ለህልፈተ ሕይወትና ለአካል ጉዳተኝነት የተጋለጡበት ጊዜ በመሆኑና በሌሎች ተያያዥ መሰል ምክንያቶች ዕለቱ በመላው ዓለም በደማቅ በዓልነት ይከበራል ታስቦም ይውላል፡፡



# የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት የዓመቱ ዓባይት ክንውኖች

አዘጋጅ፡- መለስ ታደሰ

- በስርዓተ ፆታ ዙሪያ ያለውን የተዛባ አመለካከት በመቅረፍ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አመለካከትን የሚቀይሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤ ውጤቱንም ይለካል፡፡
- የጤናውን ሴክተር ተደራሽነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የአካል ጉዳተኞችን የማካተቻ ማኑዋል በማዘጋጀት፤ የጤና ተቋማት እንዲተገብሩት የማስተዋወቅ፣ ለባለሙያዎቹ የምልክት ቋንቋን ጨምሮ ስለአካል ጉዳተኝነትን ጉዳይ እንዴት አካቶ መስራት እንደሚችሉ ስልጠና ይሰጣል፤ የመረጃ ተደራሽነትንም ለማስፋት የጤናችን ፕሮግራም በምልክት ቋንቋ ተደግፎ እንዲቀርብ የድርሻውን ይሰራል፡፡
- በጤና ተቋማት ለፆታዊ ጥቃት ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአተገባበር ሰነድና የማሰልጠኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና በመስጠት የጤና ተቋማት የተቀናጀ የአንድ መስኮት አገልግሎት የማስጀመር፣የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን መስራት
- ሴት አመራሮች በጤና ተቋማትም ሆነ በቢሮ ደረጃ ቁጥራቸው እንዲጨምርና እኩል ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የአቅም ማጎልበት ስራዎችን የመስራት፣ ሴቶች ወደ አመራር እንዲመጡ የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግና የበላይ አመራሮችም የጉዳዩ ባለቤት ሁኖ እንዲሰሩበት የማድረግ ስራ ይሰራል
- በክልልና በተጠሪ ተቋማት ደረጃ የሚገኙት መዋቅሮቻችን በማጠናከር፣የጋራ እቅድ በማቀድና በተለያዩ ስልጠናዎች እያጠናከረ የመሄድ ስራ ይሰራል፡፡
- ሴቶች፣ህፃናትን፣ወጣቶችንና አካል ጉዳተኞችን በጤናው ዘርፍ ተጠቃሚነታቸውንና ተሳታፊነታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ የማስፈፀሚያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት
- ሴቶችን ለማብቃት የሚረዱ ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት
- ሴቶችን ለማብቃት የሚረዱ ጥናቶችን ማካሄድና እንዲካሄዱ ማድረግ
- የስርዓተ-ፆታ አተገባበር ሂደትን መከታተል
- ከስርዓተ ፆታ አንፃር የታቀዱ እቅዶችን አፈፃፀም መገምገም
- የስርዓተ-ፆታ አተገባበር ሪፖርት ማዘጋጀትና ለቀጣይ ስራዎች ዕቅድ ግብዓት ማድረግ





# እፎይ እንበል አብረን!!

ወፍ ጭጭ ሲል ገና ሳይገፍ ለሊት
በድንግዝግዝ ሲታይ ወጋገን ምልክት
ጨለማው ሲተካ በተፈጥሮ ብርሀን
መንገዷን ጀመረች እምዬ አዝላኝ እኔን፡
ባዶውን ገንቦዋን አርጋ በራሷ ላይ፤
ማዶ ለመድረስ ሳይበረታ ፀሀይ።
ከተራራው ጀርባ ከውሀው ጅረት፤
በብዙ ተጉዛ ደርሳ ለመቅዳት፤
ሜዳውን ጨርሳ ስትወጣ ዳገት፤
በጨቅላ አእምሮዬ ድካሟን ዝለቷን
ደመነፍሴ አወቀው እንግልት ስቃይዋን፡
በእምዬ ታዝዬ ድካም ሳልጋራት፤
ደረሰችና በተራራው አናት፤
ከቁጥቋጦ ከአጋሙ ከአረንቋ፤
እኔን እንዳይነካኝ ተጠንቅቃ፤
እንዳይጭረኝ ተሸማቃ፤
በቁጥቋጦው ስትኳትን፤
ሰብሰብ አርጋ ቀሚሷን፤
መውረድ ጀመረች ቁልቁለቱን
ስትራመድ ችላ ሁሉን፤
እንቅፋቱን ስራ ስሩን፤
ድምጿን ሰማሁ የስቃይዋን፤
ውይይ..ይ አለች በድንገት፤
ሸብረክ ብላ እመሬት፤
አጋም እሾክ እግሯን ወግቷት
ስቃይዋ ህመሟ ገብቶኝ በደመነፍስ፤
ሆዴ ተላወሰ አለኝ አልቅስ አልቅስ
አወራጨሁ ከጀርባዋ ሰውነቴን፤
እማ... እማ..እማ እያልኩኝ
በርትቶ ስቃይዋ አልሰማች፤
እህህ...እህህ እያለች።
ፀሀይዋ በአናት ስትሆን ትክክል፤
ግለቷ ጨምሮ ስታቃጥል፤
እያነከሰች እያዘገመች ደረሰችና፤
ሸክሞቿን ከመሬት አወረደችና፤
ከፌስታሉ አምባሻ ከያዘችው ቋጥራ፤
እጇ እንደቻለላት ቆንጥራ፤
አስራብኩህ ልጄ አንጀቴ፤
አጎረሰችኝ አለችና በሞቴ።
ከረሃብ ጥማት አስታገሰችኝ፤
እሷ ሳትበላ እኔን አበላችኝ።
ደረቅ ጡቶቿን ተደግፍኩኝ
እንደ እናቴ እኔም ደክሞኝ
እንቅልፍ መሳይ ሸለብ አርጎኝ።
እሾኳን በእሾህ አወጣችና
እግሯን በቅጠል ጠቀለለችና
ውሃውን በጋኑ ቀዳችና
ከወንዙ ዳር ከሚቀዱት፤
ከሴቶቹ እዛ ካሉት፤
ስሚኝማ እህቴ! እባክሽ ወገኔ፤
ጋኑን በአናቴ ልጄንም በጎኔ፤
አሸክሚኝና ቶሎ ልሂድ እኔ።
አሸከመቻት ሴቲቱ እናቴን፤
አመቻቸችላት በማቶት ጋኑን።
ከሁለት ሸክም ጋራ በታጠፈ አንጀቷ፤
ጉዞዋን ከቤቷ እምዬ ጀመረች፤
የቆሰለ እግሯን እየጎተተች።
በረዥሙ ጉዞ በብዙ ተዳክመን፤
መንገዱ ተጋምሶ ደረስን ቀያችን።
እምዬ እናት አለም አውርዳ ሸክሞቿን፤
በአገኘችው ቦታ አስቀድማ እጆቿን፤
ወደቀች መሬት ላይ ለቅፅበት እረፍት፤
ብዙ ስራ አለባት ገና እስከውድቅት፡
እንዲህ ነበረ የእናቴ ኑሮ፤
ዘወትር ድካም ሁልግዜ እሮሮ።
ቀን አለው ለሁሉም፤
መጣልን የቀን መልካም
የእነ እምዬን ድካም፤
የሚያቀል የሚያክም።
በቧንቧ ተስቦ ከከርሰ ምድራችን፤
ኩ..ል..ል ያለ ውሃ ፈሰሰ ደጃችን፤
ኩ..ል..ል ያለ ውሃ አፈስን በጃችን።
ይባርካቸው የረዱንን፤
መረቅናቸው ከልባችን፤
ጤና ይስጣቸው ጤና ለሰጡን፤
ላቃለሉት መከራ ፍዳችንን።
እፎይ.ይ.ይ... አለች እምዬ እናት አለም፤
እኔም እፎይይ... አልኩኝ ሲቀልላት
ድካም።

እመቤት ታረቀኝ
ክሊኒካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

“የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት
ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና
ተጠቃሚነት!”

# ከአለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ወቅታዊ ሁነቶች በጥቂቱ

አዘጋጅ፡- ዘውዱ ጉሉማ

- በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣውን አዋጅ አስመልክቶ ብርካታ ተቋማት የህፃናት ማቆያን እያስገነቡ ሲሆን የፐብሊክ ሰርቪስም የመንግስት ሰራተኞች የሆኑ ህፃን ልጅ ያላቸውን እናቶች የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም የህፃናት ማቆያ ከማዘጋጀት አኳያ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ሲሆን በቅርቡ ማዕከሉ ተዘጋጅቶ ለአገልግሎት የሚውል




ይሆናል፡፡

- ፆታዊ ጥቃትና ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ወንድና ሴቶችን አገልግሎት የሚሰጠው የአንድ መስኮት አገልግሎት (የህግ፣ ስነ ልቦና ምክር፣ የህክምናና የፍትህ አገልግሎት የሚያገኙበት ማዕከል) በተለያዩ የክልል ሆስፒታሎች ለማስፋፋት የልምድ ልውውጥና የባለሙያ ስልጠናዎች በስፋት እየተሰጡ ይገኛሉ፡፡
- በጤና ሚኒስቴር የሴ/ህ/ወ/ጉ/ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት በተለያየ ደረጃ ከሚገኙ በጎ ፍቃደኛ ሰራተኞች የተሰበሰቡ በርካታ የንጽህና መጠበቂያ ሞዴሶች፣ ሳሙናዎች፣ ሶፍቶች፣ የተለያዩ አልባሳትና ጫማዎች ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸውና በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ድጋፍ አደረገ፡፡





- በዚህ በያዝነው ዓመት በተፈጠረው የአለመረጋጋት ችግር በመነሳሳት በርካታ እናቶችን ባሳተፈ መልኩ ጀግኒት የሰላም ኮንፈረንስ በተለያ ክልሎች በመዟዟር የሰላምን ጥቅምና አስፈላጊነት ላይ መወያየት ተችሏል፡፡
- ከበጎ ፍቃደኞች የተሰበሰበ መጠኑ ከአስራ አንድ ሺ በላይ የሚሆን የገንዘብ መጠን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲሰቲ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የካንሰር ህሙማን ማዕከል ድጋፍ ተደርጓል፡፡ማዕከሉ ለበርካታ ሴቶች፣ ህፃናትና አረጋውያን የካንሰር ህክምና አገልግሎትን በአስቸጋሪ ሁኔታዎችና ችግሮች መካከል የሚሰጥ በመሆን ብሎም የካንሰር ህክምና አገልግሎት በብዛት ተጠቃሚዎች እድሜያቸው ከወራት ጀምሮ ከስልሳ ዕመት በላይ ለሚሆኑ አዛውንቶች የሚሰጥ ነው፡፡
- በዚህ በያዝነው በጀተ ዓመት በርካታ እውቀትና ብቃት ያላቸው ሴት ሚኒስትሮች ወደ ኃላፊነት የመጡበት ሁኔታ ያለ ሲሆን በተለይ ቁልፍ በሚባሉ የመንግስት የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሴቶች መሰየማቸውና መወከላቸው ሀገሪቷ ከዚህ ቀደም ባልተለመደ ሁኔታ በሴቶች ላይ እያሳደረው ያለው እምነት ከፍተኛ መሆኑም ከማሳየቱ ባለፈ ሴቶች ዕምቅ አቅማቸውንና ችሎታቸውን አውጥተው እንዲጠቀሙ እያስቻለ ሲሆነ በተጨባጭም ወደኃላፊነት ከመጡ ብኃላ በርካታ አመርቂ ውጤቶችን እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡



- በዚሁ በያዝነው በጀተ ዓመት ውስጥ በክልሎች ላይ የታየው ከፍተኛ የሰላምና አለመረጋጋት መኖሩና ግጭትና ብጥብጥ በየአከባቢው መነሳቱ በከፍተኛ ደረጃ ሴቶች ላይ የደረሰ በርካታ ፆታዊ ጥቃት አስገድዶ መደፈርና ለስደት መጋለጣቸው ከፍተኛ ጫና ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሴቶችና ልጃገረዶች በየጊዜው በሚፈጠሩ የግጭትና አለመረጋጋት ችግሮች ዋነኛ ገፈት ቀማሾች ናቸው፡፡
- በፌዴራል ጤና ሚኒስቴር የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን አማካኝነት በቀረበው ጥያቄ መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሲጋራ ማጨሻ ስፍራን የሚገድብና አልኮልን በብሮድካስት ሚድያ ማስተዋወቅ የሚከለክለውን አዋጅ አፀደቀ፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባካሄደው 4ኛ ዓመት የስራ ዘመን 24ኛ መደበኛ ስብሰባው ነው አዋጁን ያፀደቀው፡፡ በፀደቀው አዋጅ ላይም መስሪያ ቤቶች፣ ጤና ተቋማት እና የወጣቶች መዝናኛ በሚገኙባቸው አከባቢዎች 100 ሜትር ርቀት ውስጥ ሲጋራ ማጨስ ክልክል መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም ማንኛውንም የአልኮል ምርት በብሮድካስት ሚድያ ማስተዋወቅ እንደማይቻልም አዋጁ ደንግጓል፡፡ በተጨማሪም




ከአልኮል መጠጦች ጋር በተያየዘም ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ታዳጊዎች አልኮል መሸጥ ክልክል መሆኑም ተገልጿል።

- በአለማችን ላይ በሴቶች ላይ የሚደርሱ የመገለልና የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች በርካታ ሲሆኑ በቅርቡ በፊሊፒንስ የተሰማው ነገር እጅጉን የሚያሳዝን ነበር። በፊሊፒንስ ሀገር ሴቶች የወር አበባቸው ሲመጣ የሚገለሉበትና የወር አበባቸውን ጨርሰው እስኪወጡ በሚቆዩበት ደሳሳ ጎጆ ውስጥ የነበረች አንዲት ሴት የተከሰተውን ከፍተኛ ቅዝቃዜ ለማጥፋት በአቀጣጠለችው የከሰል/እንጨት ጭስ አማካኝት የአየር ዕጥረት ታፍና መሞቷ ተዘግቧል። በዚህ አከባቢ ያሉ በርካታ ሴቶች በወር አበባ ወቅት ከቤት በሚገለሉበት ወቅት በሚከሰቱ የአውሬ መበላትና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ምክንያት ይሞታሉ።
ምንጭ፡-https://womenintheworld.com/2019/02/04/yet-another-nepalese-woman-dies-in-menstruation-hut/



- እንደ ፎርብስ መጽሔት ገለፃ ወ/ሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ በአለማችን ላይ ከሚገኙ አንድ መቶ ሴት ተፅእኖ ፈጣሪዎች መካከል አንዷ ሆኑ የጀርመኗ መራሂተ መንግስትና የእንግሊዟን ጠቅላይ ሚኒስቴርን በቀዳሚነት ደረጃ ያወጣው ይሄው መጽሐት የኢትዮጵያዊቷን ፕሬዝደንት በፖለቲካው ዘርፍ ተጽእኖ እየፈጠሩ የሚገኙ ሲልም አሞካሽቷል።
ምንጭ፡-https://www.forbes.com/power-women/list/#tab:overall
- “ምን ለብሳ ነበር” “What She Wore” የተሰኘ አውደ ራዕይ ተካሄደ። በዩ.ኤ.ን ዉመን ደጋፊነት በአዲስ አበባ ሲዊዲን ኤንባሲ የተደረገው “ምን ለብሳ ነበር” “What She Wore” የተሰኘና የበርካቶችን ቀልብ የሳበው አወደ ራዕይ የተዘጋጀው አስራ ስድስቱ (16ቱ) ቀናት የጸረ ፆተዊ ጥቃት/ ወሲባዊ ጥቃት ዘመቻን ታሳቢ አድርጎ ነው። ጥቃት ፈፃሚዎቹ አብዛኛውን ጊዜ ጥቃቱን የሚፈጽሙት በማንኛውም ሴቶች ላይ እንደሆነና ጥቃት ለመፈጸም የሚያነሳሳቸው የሴቶች አለባበስ፣ የዕውቀት ደረጃ፣ ዕድሜና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች ሳይሆን ጥቃት የሚፈጸምባቸው ሴት በመሆናቸው ብቻ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።




## የስርዓተ - ፆታ እኩልነት አትኩሮት በተመሳሳይነት ወይስ በልዩነት?

አዘጋጅ፡- ትሁት አየለ

ታሪክ እንደሚያሳየው ለረዥም ዘመናት ሴቶች በወንዶች ድምፅና ተሳትፎ ሲወከሉ ቆይተዋል። ይሄም በሴቶች ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ሰንብቷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በሌላ በኩል ሰዎች ዘንድ የሴቶች ተሳትፎ እኩል መሆን እንዳለበት እሙን ቢሆንም በዛ ልክ ተቀባይነት ኖሮት ወደ እኩልነት የሚያደርስ የመሻሻልና የዕድገት እንቅስቃሴ ውጤታማነት ጎልቶ አይታይም። የስርዓተ-ፆታ እኩልነት እድገት/መሻሻል እንዲመጣ የማህበረሰቡ አስተዋጽኦ ከሀገር ሀገር ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የሚለያይ እና ከፍተኛ ነው። በወንድ እና በሴት መካከል በአዕምሮ ብቃት ምንም ልዩነት የሌለ ቢሆንም፤ በማህበራዊ መስተጋብር የሚታዩ ልዩነቶች እንዲከሰቱ ምክንያት የሆኑት ማህበራዊ ልማዶች፣ ጫናዎች እና የተዛቡ አመለካከቶች ናቸው። በእርግጥ እነዚህ ነገሮች በመኖራቸው




በሴቶች የስርዓተ-ፆታ ሚና እና የራስ ምስል/ ለራስ የሚሰጥ ግምት/ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ጥርጥር የለውም። በዚህ መሰረት ወንዶችና ሴቶች ተመሳሳይ እንደሆኑ በማሰብ ተመሳሳይ በሆኑ መንገዶች ብቻ ማየት እውነተኛ የሆኑ የስርዓተ-ፆታ ልዩነቶችን በመካድ እኩልነትን ለማምጣት ትኩረት መደረግ ያለባቸውን ጠቃሚ ነጥቦች እንደማስወገድ ይወሰዳል። ከሴቶች አንፃር የእኩልነት ጽንሰ ሀሳብ ሁለት ስለት



እንዳለው ሰይፍ ይታያል። በእኩልነት መርህ ሴቶች ከወንዶች እኩል የሰብአዊ መብት፣ ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው ቁሳቁሶች፣ አጋጣሚዎች/እድሎችና ሃብትን/ ግብዓትን የማግኘትና በእነዚህም የመደሰት/ የመጠቀም አጋጣሚን በከፊልም ቢሆን ማግኘት ችለዋል። ይሄም በማህበራዊ ግንኙነት የሚታየውን የሴቶች የዘፈቀደ አያያዝ ያስወግዳል።


ይሁን እንጂ የመጀመሪያው የእኩልነት ጽንሰ-ሃሳብ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያሉትን የተለያዩ ልዩነቶች አቃፊ አልነበረም፡፡ እውነታው እንደሚያስረዳው የተመሳሳይነት መርህ ከእኩልነት አስተሳሰብ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ ማህበረሰባዊ ስርዓቱ የሚሰራው በዚህ መልክ ነው በወንድና በሴት መካከል ያለውን ልዩነት ከግምት ሳያስገባ ተመሳሳይ በሆኑ መለኪያዎች እንዲታዩ ያደርጋል ይሄም ሁሉም ሰው የሰው ልጅ ወካይ እንደሆነ በማመን፡፡ በሌላ አገላለፅ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የእኩልነት ጥያቄ የሚመሰረተው በሴቶችና ወንዶች በተግባቡት የእርስ በእርስ ተቀባይነት መሆኑ ነው፡፡

እኩልነት እና ልዩነት ተዛማጅ ጽንሰ-ሐሳቦች ናቸው፡፡ ይህ ማለት እኩልነት እና ልዩነት በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያሉ ጽንሰ-ሐሳቦች ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ, ልዩነት የእኩልነት ሌላኛው ገፅታ ተደርጎ ተቆጥሯል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ እይታ አዎንታዊ ፍቺ ያለው ሲሆን ሌላኛው ደግሞ አሉታዊ ፍች ይኖሩታል፡፡ ከሁለቱ ዕይታዎች ተቀባይነቱ የሚያመዝነው ልዩነትን ከግምት በማስገባት ዕኩልነትን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ አተያይ ያለው ነው፡፡



በዚህ ረገድ በሴቶችና ወንዶች ቡድኖች ላይ የሚስተዋሉ ተፅእኖዎችን የሥርዓተ-ፆታ ትንተና በማድረግ ተለይተው የሚታወቁ ፍላጎቶች ላይ ትኩረት በማድረግ የተለያዩ የሥርዓተ-ፆታ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት ሥርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል ያለበት ሥር የሰደደ የሥርዓተ-ፆታ ሥርዓትን የሚገዳደረው ሥር የሰደደው ሥርዓት ከግብዓቶችና ትምህርት እጥረት፣ ለረሃብና ጥቃት ተጋላጭነት ወዘተ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ እነኚን ልዩነቶች ማስተዋል ለስርዓቱ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት እኩልነትን ለማምጣት አጋዥ ይሆናል፡፡

የእኩልነት ሌላው እትም እንደ አዎንታዊ እሴት ስለ እኩል ሀብት ባለቤትነትና ተጠቃሚነት ይናገራል. ይህ ማለት ባለይዞታ መሆን ማለት ነው ተመሳሳይ ወይም በእኩል የሚታወቁ ማህበራዊ ሀብቶች አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ እኩልነት እንዲኖር ለማድረግ መፈናቀልን ማስወገድ ይጠበቃል፡፡ የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች፣ ልማዶች፣ ግንኙነቶችና ልማዳዊ አባባሎች ሴቶችና ወንዶች የሚኖራቸውን ግምት እንዲሁም የሃብት ባለቤትነታቸውን ሁኔታ ይወስናሉ፡፡ ለምሳሌም ሴቶች በዝቅተኛ ክፍያ ወይም ፈጽሞ ያለምንም ክፍያ ወይም መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ ተሰማርተው ህፃናትን፣ የታመሙትን፣ ሽማግሌዎችንና አካል ጉዳተኞችን በመንከባከብ አብዛኛውን የምርታማነት እድሜያቸውን ያሳልፋሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ መሆናቸው ከአሰሪዎቻቸው



የሚገኙ የጡረታና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች እንዲገለሉ ያደርጋቸዋል፡፡

ከትክክለኛው የእርስ በእርስ ማህበራዊ ግንኙነት ማዕቀፍ ሊካተት የማይገባው ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚገኙ ጥቂት የስራ ድርሻ/ተግባራት የሚከለክሉ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ይሄም አንዳንድ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ፆታን መሰረት ያደርጋሉ ብሎ ማሰብ ነው፡፡ ሴቶችና ወንዶች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ መሆናቸው ሊታመን ይገባል፡፡ ወንድና ሴት በተለያየ ጥንካሬ፣ ስጦታዎች እና ተሰጥኦዎች እርስ በእርስ የተደጋገፉ ናቸው እንጂ እንደ አንዳንድ የተዋጣለት ተቀናቃኞች ሊታዩ አይችሉም፡፡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ተመሳሳይ አይደሉም ነገር ግን ብዙ የጋራ ነገሮች አሏቸው፡፡ ተፈጥሯዊ ሀቅ እንደሚያረጋግጠው፣ በባህርይ የተለየ ምንም አይነት ባህርይ ያልነበረው ነገር ቢኖር ወንድ ወይም ሴት ብቻ ነው፡፡ በአጠቃላይ ልዩነት እኩልነትን ከማምጣት አንፃር ከዕኩልነት ጋር ተደጋጋፊ ፅንስ ሃሳብ ነው፡፡

## "ላንቺ"

*ዋንጫ ይገባሻል ለዚያውም የወርቅ፣*
*ዳግም ያንገት ኃብል የሚያብረቀርቅ፣*
*ከአልማዝ የተሰራ ከከበረ ድንጋይ፣*
*እንቁ ይቅረብ ይሆን ውብ ፍቅሬን የሚያሳይ?*
*ገንዘብ ከሚገዛው ከአለም መሰላል፣*
*ከወዲያኛው ጥግ የሚበራ ፀዳል፣*
*ከድምሩ መሀል የላቀው ተመርጧል፣*
*ቀንና ለሊቱን ከበሮ 'ሚመታው ድምፅ አልባው ቃጭል፣*
*ላንቺ የሚገባው ውስጤ 'ተቀመጠው ልቤ ይሻልሻል፣*
*ኃላም ልሀቀት ጨምሮ ይዞሽ ይቀበራል፡፡*

አልማዝ ሰይድ አመዴ(ሲ/ር)
ነርስ ስፔሻሊስት ከፍተኛ ኦፊሰር III
ጤና ጥራት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

# ድንቃ ድንቅ

አዘጋጅ፡- ዘውዱ ጉሉማ

- በአለማችን ላይ በአማካይ በአንድ ቀን (24 ሰዓት) ውስጥ 535,000 — 365,000 በላይ ህፃናት ይወለዳሉ፡፡
- በቀን ውስጥ በአማካይ በአለም ላይ 5.6 ሚሊዮን የመብረቅ ነጎድጓድ ይፈጠራል፡፡
- በቀን ውስጥ በአማካይ ሁለት በህይወት የሚኖሩ ፍጥረቶች የሚተነፍሱትን አየር ከአንድ ዛፍ ያገኛሉ፡፡
- በአንድ ቀን (24 ሰዓት) ውስጥ 18 ሚሊዮን የሚደርሱ የአለማችን ህዝቦች ልደታቸውን




ያከብራሉ፡፡
- በቻይና በአማካይ 510 ቶን የሩዝ ምርት በየቀኑ ይሰበሰባል፡፡
- በአለም ላይ ከሚገኙ አጠቃላይ ዶሮዎች ውስጥ በአማካይ በአንድ ቀን (24 ሰዓት) ውስጥ 190 ሚሊዮን እንቁላል ይመረታል፡፡



- በአለም ላይ 67,000 ዛፎች በአማካይ በአንድ ቀን ውስጥ የሚቆረጡ ሲሆን ይህም 46,000 ለወረቀትና ለቦርሳዎች የሚውል ሲሆን 21,000 ደግሞ ለመጸዳጃ ቤት ሶፍትነት የሚውል ነው፡፡
- በምድራችን ላይ የሚገኙ ህዝቦች በአንድ ቀን (24 ሰዓት) ውስጥ በአማካይ ከ15 ጊዜ በላይ ይስቃሉ፡
- የእያንዳንዱ ሰው ልብ በአማካይ በቀን ውስጥ ከ104,000 በላይ ይመታል፡፡
- በአማካይ የአለማችን ህዝቦች በቀን ውስጥ 16 የአሜሪካን ዶላር ያገኛሉ
- ማንኛውም አዋቂ ሰው በቀን (24 ሰዓት) ውስጥ ከ23,000 ጊዜ በላይ ይተነፍሳል፡፡
- ከአጠቃላይ የአለማችን ህዝቦች በአማካይ አንድ ሰው በቀን ውስጥ እስከ 8,000 እርምጃ በላይ ይራመዳል፡፡
- በአማካይ እያንዳንዱ ሰው በቀን ውስጥ ለ12 ደቂቃ ይታጠባል፡፡
- በአለማችን ላይ ያሉ መደብሮች በአማካይ ከ15 ሚሊዮን በላይ ፓኮ ትምባሆ/ ሲጋራ በቀን ውስጥ ለደንበኞቻቸው ይሸጣሉ፡፡



- በአማካይ በሰውነት ውስጥ የሚገኙ ህዋሳቶች/ ሴሎች ጊዜያቸው አልፎ/ አርጅተው የሚሞቱ ሲሆን ከ50 ትሪሊዮን በላይ ሴሎች በድጋሚ ይፈጠራሉ፡፡
- በምድር ላይ የሚገኙ ህዝቦች በአማካይ ከ48,000 ቃላቶችን በቀን ውስጥ ይናገራሉ፡፡
- በቀን በአማካይ 30,000 በላይ ህዝቦች በአለማችን ላይ ይፋቀራሉ፡፡
- በአለማችን ላይ የሚኖሩ ህዝቦች መጸዳጃ ቤት ከተጠቀሙ በኃላ በአማካይ ከ22 ቢሊዮን ጊዜ በላይ ውኃ ወደ መጸዳጃው ውስጥ የሚደፉ/ የሚለቁ ሲሆን ይህ ማለት በአማካይ በቀን ውስጥ የሚለቀቀው ውኃ ከ50 በመቶ በላይ ለሚሆን የአለማችን ህዝቦች በበቂ ሁኔታ የውኃ አቅርቦት ፍላጎታቸውን ሚሟላት የሚያስችል ነበር፡፡
- ከ110,000 በላይ ሰዎች በአማካይ በቀኑ ስራቸውን ይቀይራሉ ወይም አዲስ ስራ ይይዛሉ፡፡

ምንጭ፡-https://www.elitereaders.com/26-amazing-things-world-one-day/?cn-reloaded=1
www.theodysseyonline.com/amazing-things-that-are-happening-in-the-world-right-now

## በዓለም ላይ ጠንካራዋ ሴት

የፖላንድ አትሌቲክስ ቡድን አባል የሆነችው አኔታ ፍሎሪካዚ በቅጽል ስሟ ሁሉም ሰው የሚያውቃት "ጠንካራዋ ሴት" በማለት ነው፡፡ አኔታ ሴቶች በብዛት ከሚተገብሯቸው ስራዎች ለየት ባለ መልኩ ብቃትና ችሎታዋን የምታሳየው መኪና ማንሳትና መጎተት፣ የክብደት ማንሳት ውድድር ላይ መሳተፍ እና ሌሎች መሰል ውድድሮች ላይ የምትወዳደርና ብቃቷን የምታሳይ ሴት ናት፡፡ አኔታ በአጠቃላይ ከ500 ኪ.ግ የሚመዝን ክብደት በአንድ ጊዜ ማንሳት መቻሏ ለየት ያደርጋታል፡፡

በእርግጥ በአለም ላይ ካሉ ሴቶች አኔታ ብቻ ሳትሆን ጠንካራ ሌሎችም ጠንካራ ሴቶች ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን እሷ ለየትና አስገራሚ በሆነ መልኩ አኔታ በአለም የድንቃ ድንቅ መዝገቦች ላይ ስሟ ሊሰፍር የቻለው ሰዎችን በማንሳት ባደረገችው ውድድር ሲሆን በሁለት (2) ደቂቃ ውስጥ አስራ ሁለት (12) አዋቂ ወንዶችን አንስቶ በመወርወር የአለምን ክብረ ወሰን በእጇ ውስጥ ማስገባት መቻሏ ነው፡፡





# የኢትዮጵያ ሴቶች ትንሳኤ

አዘጋጅ፡- አቤል ሞሴ

## ጀግኒት


አለመች ፣ አቀደች ፣ አሳካች ።

የስኬታማ ሴቶች ህይወት፣ ለኢትዮጵያ ወጣት ሴቶችና ልጃገረዶች (ለሌላውም አለም ጭምር)፣ መንፈስን የሚያነቃቃ አርአያ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን:: እነዚህ ስኬታማ ሴቶች፤ በአጥር የተከለለውን ልማዳዊ የህይወት አለም አሜን ብለው ሳይቀበሉ ድንበሩን በመግፋትና በመገርሰስ፣ በተለያየ መንገድ ለራሳቸውና ለሌሎች፣ አዳዲስ የህይወት አማራጮችን የቀየሱ የጀግንነት ተምሳሌት ናቸው:: የተወለዱበትና ያደጉበት አውድ፣ እንዲሁም የመጡበት የህይወት መንገድ… የተለያየ ነው:: ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከአገር ቤት እስከ ዳያስፖራ አመጣጣቸው ለየቅል ቢሆንም፣ ለኢትዮጵያ ሴቶች በርካታ የስኬት አማራጮችን በመፍጠር ውጤታማ ለውጥ ያስመዘገቡ ሴቶች ናቸው ፤ በቤተሰብም ሆነ በማህበረሰብ፣ በአገርም ሆነ በአለም ደረጃ:: ጥቂቶቹ በቀድሞው የአገራችን ታሪክ የሚታወቁ ሲሆኑ፤ አብዛኞቹ ደግሞ የዘመናችን ሴቶች ናቸው:: ነገር ግን ሁሉንም የሚያመሳስላቸው የጋራ መለያ አላቸው:: ጠንካራና ብርቱ፣ ደፋርና ቁርጠኛ፣ እንዲሁም ብዙዎቹ ለወገኖቻቸው አንዳች ፋይዳ ለማበርከት እጅጉን የተጉ ሴቶች ናቸው:: የእነዚህ ጀግኒት ታሪክ፣ የእስከዛሬውን ስኬት ከማሳየት አልፎ፣ ወደፊትም ኢትዮጵያና መላው አለም ገና ብዙ አጃኢብ የሚያሰኝ ተአምር እንደሚጠብቃቸው የሚጠቁም ነው:: እንዴት ቢሉ፣ እያንዳንዷ የኢትዮጵያ ወጣት ሴት ምቹ ሁኔታ አግኝታ እምቅ አቅሟን በሙሉ አውጥታ የተነሳች ጊዜ፣ እልፍ የስኬት (የእመርታ) ታሪክ ይፈጠራል:: በመሆኑም ከእነዚህ ጀግኒት መካከል ከድሮዎቹ እና ከአሁኖቹ ሁለት ጀግኒቶችን መርጠን በዚች አጭር ቅኝት ረጅሙን ህይወታቸህውን ልናስቃኛችሁ ወደድን፦ መልካም ንባብ::

## ምንትዋብ (ንግስት:እቴጌ)

አስልታና አርቃ የምታቅድ፣ የሰዎችን ቀልብ የምትይዝ ብርቱ የኢትዮጵያ ንግስት፣ የአፄ በካፋ ሚስት፣ የልጇ የአፄ ኢያሱ ዳግማዊ እንዲሁም የልጅ ልጇ የአፄ ኢዮአስ ቀዳማዊ ሞግዚት (እንደራሴ)፤ የጎንደር ነገስታት ዘመን ማብቂያ ላይ የገነነች የፖለቲካ ተዋናይ፣፤ የኪነ ጥበብ በተለይም የሥነ ሕንፃና የሥነ ሥዕል ተቆርቋሪ አለኝታ በመሆን የቤተመንግስትና የቤተክርስትያን ሕንፃዎችን ያስገነባች ንግስት፤ እቴጌ ምንትዋብ የተወለደችው እ.ኤ.አ 1706 ቋራ በሚባል ስፍራ ነው:: ንግስት፣ የአፄ በካፋ ሚስት፣ የልጇ የአፄ ኢያሱ ዳግማዊ እንዲሁም የልጅ ልጇ የአፄ ኢዮአስ ቀዳማዊ ሞግዚት (እንደራሴ)

ገና በሕፃንነቱ ከነገሰው ልጇ ከኢያሱ ጋር ዙፋን ተጋርታ ዘውድ የደፋችው ንግስት ምንትዋብ፤ የልጅ ልጇ ከነገሠ በኋላም ጭምር የሞግዚት እንደራሴነቷ ሳይቋረጥ፣ ለ40 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን በበላይነት ገዝታለች:: ባለቤቷ አፄ በካፋ፣ እ.ኤ.አ በ1730 በሞተበት ወቅት በሀያዎቹ የእድሜ ክልል የነበረችው ወጣት ምንትዋብ፣ ሴት መሪዎች ባልነበሩበት በዚያ ዘመን የፖለቲካ መዘውሩን በመጨበጥ ስድሳ አመት እስኪያልፋት ድረስ በአገር መሪነት ዘልቃለች:: ውበቷ እንደ ሥሟ ወደር የለሽ ነው ከሚለው ውዳሴ በተጨማሪ በአእምሮ ብቃቷና በብልህነቷ አድናቆትን ያተረፈች የፖለቲካ ጥበበኛ እንደሆነች ስራዎቿ ይመሰክራሉ:: በራሷና በቤተሰቧ የተያዘውን ስልጣን ለረዥም ጊዜ ለማቆየት፣



የቅርቡንና የሩቁን እያሰላች ብልጠት በተሞላበት መንገድ፣ የምታምንባቸው ወገኖቿን ለቁልፍ የስልጣን ቦታ አብቅታለች፤ ከአጎራባች ገዢዎች ጋር ሽርክና ፈጥራለች:: በሥነ ጥበብ እና በሥነ ሕንፃ አለኝታነቷ፣ በዋና ከተማዋ በጎንደርና በአካባቢዋ፣ በማራኪ የዘመነ ጎንደር ውበታቸው የሚታወቁ፣ በርካታ የቤተመንግስትና የቤተክርስትያን ሕንፃዎችን አስገንብታለች:: የልጅ ልጇ አፄ ኢዮአስ በነገሠበት ዘመን፣ በአያትነቷ የሞግዚት እንደራሴ ሆና ስልጣን ላይ ብትቆይም፣ የኋላ ኋላ ሃያል ባላጋራ ገጥሚታል — የንጉሡ እናት የስልጣን ተቀናቃኝ ሆና መጣችባት:: ምንትዋብ የስልጣን መንበሯን ይዛ ለመቀጠል አስልታ እንደወተሮው በዘረጋችው መረብ ነው የራሷን ውድቀት የደገሰችው:: በንጉሡ አያት እና በንጉሡ እናት መካከል የተፈጠረው የፖለቲካ

ፍጥጫ፣ ወደ ግጭትና ወደ ጦርነት ሊያመራ ሲል፣ ከትግራይ ራስ ሚካኤል ስሁል ለሽምግልና እንዲመጣ የጠራችው ራሷ እቴጌ ምንትዋብ ነች። ሚካኤል ስሁል ግጭቱን ቢያበርድም አፄ ኢዮአስን ገድሎ ስልጣኑን ተቆጣጠረና፤ የምንትዋብ ስልጣን ብቻ ሳይሆን የያኔው የጎንደር ነገስታት ዘመንም አበቃለት፤ የዘመነ መሳፍንት መባቻም ሆነ። ዘመነ መሳፍንት አጭር ጊዜ አይደለም፤ አፄ ቴዎድሮስ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ስልጣን እስከያዘበት ጊዜ ድረስ ብዙ አመታትን አስቆጥሯል።

ከጣና ሀይቅ በስተምዕራብ፣ እስከ ሱዳን ድንበር በተዘረጋው የቋራ ክፍለ ግዛት፣ በ18ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ እ.ኤ.አ በ1706 ዓ.ም እንደተወለደች የሚነገርላት ምንትዋብ፤ አባቷ ደጃዝማች መንበረ የደንቢያው ባላባት ሲሆን፣ እናቷ ወይዘሮ እንኮዬ ደግሞ የመሳፍንት ተወላጅ ነች። ከሁለት መቶ አመታት ቀደም ብሎ ኢትዮጵያን ሲገዛ ከነበረው ከአፄ ሚናስ የሚመዘዘው ንጉሣዊ የትውልድ ሀረግ ምንትዋብ ላይ የሚደርሰው በእናቷ ወገን ነው። ብዙ ሳትቆይም፣ በጋብቻ ሌላ የንጉስ ቤተሰብ ውስጥ ገባች። የመጀመሪያ ሚስቱን በሞት ያጣው አፄ በካፋ፣ የ16 አመቷን ምንትዋብ እ.ኤ.አ በ1722 ዓ.ም ወደ ቤተመንግስቱ አምጥቶ አገባት። አመት ቆይታ ወንድ ልጅ፤ ከዚያም ሴት ልጅ ወለደች። በጎን ከጋብቻ ውጭ፣ መልምል ኢያሱ ከሚባል የንጉሡ የወንድም ልጅ ጋር በነበራት የፍቅር ግንኙነት፣ ሶስት ሴቶችን እንደወለደችም ይነገራል።

የፖለቲካውንና የስልጣን መውጫ መግቢያውን አብጠርጥራ ለማወቅ ጊዜ ያልፈጀባት ምንትዋብ፤ ባለቤቷ አፄ በካፋ እ.ኤ.አ በ1730 ዓ.ም በሞተ ማግስት ነው፣ በ24 አመት እድሜዋ አገር መግዛት የጀመረችው። የ7 አመት ህፃን የነበረው ልጇ፣ “አፄ ኢያሱ ዳግማዊ” ተብሎ ዙፋን ላይ ሲወጣ፤ ምንትዋብም የዙፋኑ ተጋሪና ሞግዚት እንደራሴ ሆና ዘውድ ደፋች። “ብርሃን ሞገስ” የሚል የዙፋን ስምም ተሰጣት። ሞግዚት እንደራሴ በመሆን የያዘችው ስልጣን ግን፤ በጥቂት አመታት ውስጥ የሚያበቃ አልነበረም። አፄ እያሱ የአዋቂ እድሜ ላይ ከደረሰ በኋላም፣ ስልጣኗን አላስረከበችውም። የልጅ ልጇ አፄ ኢዮአስ በነገሡባቸው አመታትም ጭምር፤ የምንትዋብ ስልጣን አልተቋረጠም። ወንድሟን ጨምሮ ከጎኗ ባሰለፈቻቸው ወገኖቿ እየታገዘች፤ ለአርባ አመታት ያህል፤ የጎንደር ነገስታት ዘመን እስካበቃበት የዘመነ መሳፍንት መባቻ ድረስ፣ ምንትዋብ አገሪቱን ገዝታለች።

ከብሩህ አእምሮ ጋር፣ ትልቅ ትልቁን የማለም ድፍረት የነበራት ምንትዋብ፣ ባለቤቷ አፄ በካፋ በህይወት በነበረበት ጊዜ ነው፣ የሩቁን አቅዳ የቀርቡን አስልታ መረብ መዘርጋት የጀመረችው። ማራኪ ሰብዕናዋንና ቤተመንግስት ውስጥ የገነባችውን ተሰሚነት በመጠቀም የመሰረት ድንጋይ ማበጃጀት ያዘች። ወደፊት አገሪቱን የመግዛት አላማዋን ለማመቻቸት የሚችሉ ወገኖቿን እየመረጠች ከወዲሁ የስልጣን ቦታ እንዲይዙ አድርጋለች። በአፄ በካፋ ዘመን በተፈጠረው የሃይማኖት ብጥብጥና የቤተክህነት ሽኩቻ ውስጥ የምንትዋብ እጅ እንደነበረበት የሚናገሩ ታሪክ ፀሃፊዎች፤ ቅባት የተሰኘውን የክርስትና አስተምህሮ ትከተል እንደነበረና ባለቤቷ አፄ በካፋ የተዋህዶ አስተምህሮውን እንዲተው እንዳግባባችው ይናገራሉ። ምንትዋብ እንደ ፈረንጅ የመልኳን ንጣትና የካቶሊክ እምነት ዝንባሌዋን የወረሰችው ከፖርቱጋላዊ አያቷ ነው የሚል ወሬ ይናፈስ እንደነበር ስኮትላንዳዊው ተጓዥ ጀምስ ብሩስ ይጠቅሳል። የሃይማኖት ሽኩቻው በምንትዋብ የስልጣን ዘመንም ታይቷል።

ከባለቤቷ ህልፈት በኋላ ወደ ስልጣን የወጣችው፤ ለህፃን ልጇ ለዳግማዊ ኢያሱ ሞግዚት (እንደራሴ) እና የዙፋን ተጋሪ በመሆን ነው ቢባልም፤ ልጇ የአዋቂ እድሜ ላይ ከደረሰ በኋላም ራሱን ችሎ አገር እንዲገዛ እድል አልሰጠችውም። የስልጣን መንበሯን



እንዳደላደለች፤ የቅባት አስተምህሮ በቤተመንግስትና በቤተክርስትያን ብቸኛ ሃይማኖታዊ ቀኖና እንዲሆን ወሰነች። በነገስታቱ መዲና ከጎንደር የአገር ግዛት ስልጣኗን ለማጠናከር፤ በፖለቲካ ስሌት ልጇ እያሱና የወሎ ኦሮሞ ተወላጅ የሆነችው ውቢት (ወለተ ቤርሳቤህ) በጋብቻ እንዲተሳሰሩ አደረገች — ከወሎ ኦሮሞ ተወላጆች ወታደራዊ አቅም ለማግኘት በማሰብ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ፤ የወሎ ኦሮሞ ተወላጆች፤ የስልጣን መቆናጠጫ በማግኘት ቀስ በቀስም ዋና የፖለቲካ ድርሻና ሚና ተቀዳጅተዋል። ዳግማዊ ኢያሱ እ.ኤ.አ በ1755 ከሞተ በኋላ፤ ቀዳማዊ ኢዮአስ ዙፋኑን ወረሰ፤ አያቱ ምንትዋብም የሞግዚት እንደራሴና የዙፋን ተጋሪ በመሆን ስልጣኗን እንደያዘች ቀጠለች። ነገር ግን፤ ተቀናቃኝ መጣባት። ከምንትዋብ ፊት ውቢት ቆመች — የቀድሞው ንጉሥ የኢያሱ ሚስትና የኢዮአስ እናት ናት። ውቢት (ወለተ ቤርሳቤህ) ጊዜው የኔ ነው አለች። የልጄ የኢዮአስ ሞግዚትና እንደራሴ ሆኜ ስልጣን መያዝ አለብኝ አለች። በሁለቱ

ሴቶች መካከል የተፈጠረው ተቀናቃኝነት፤ ከእነሱ አልፎ እየሰፋ የቋራ እና የወሎ ኦሮሞ ተወላጆች ግጭት ወደ መሆን ተሸጋገረ:: የስልጣን መንበሯ አደጋ ላይ የወደቀባት ምንትዋብ፣ ዘመናዊ ጠመንጃ የታጠቀ ብዙ ጦር ያደራጀውን ራስ ሚካኤል ስሁልን ከትግራይ ለመጥራት ወሰነች:: የስልጣን ግብግቡን ለማብረድና ደም አፋሳሽ ግጭትን ለማስቀረት ብቻ ሳይሆን፤ የስልጣን መንበሯንም መልሳ ለማጠናከር እንደምትችል ምንትዋብ ተስፋ ነበራት:: እንዳሰበችውም ራስ ሚካኤል፤ ግብግቡን በማብረድና ግጭቶችን በአጭሩ በመቅጨት ሰላም ለማስፈን ችሏል:: ለዚህም ከንግስና በታች የመጨረሻው ከፍተኛ ማዕረግ ተሰጥቷቸው “ራስ ቢትወደድ” ተብለዋል:: ነገር ግን የምንትዋብ ሃሳብ አልተሟላም:: በተቃራኒው የፈራችው ደረሰ፤- ከፈራችውም በላይ እንጂ:: ራስ ሚካኤል ጎንደር ውስጥ ሰላም ፈጥሮ በሰላም ለመሰናበት ፈቃደኛ አልሆነም:: አፄ ኢዮአስን በመግደል፤ መንበረ ስልጣኑን ተቆጣጠረ:: የምንትዋብ የስልጣን አመታት የተቋጨውና ለምእተአመት የሚዘልቀው ዘመነ መሳፍንት የተጀመረው በዚህ ጊዜ ነው::

በልጅ ልጇ መገደል ቅስሟ የተሰበረው ምንትዋብ፤ ጎንደርን ለቅቃ ወደ ቁስቋም በመሄድ ለብቻዋ ወደ ተገለለ ኑሮ ገባች :: እስከ ህይወቷ ፍፃሜ ድረስ:: ህይወቷ ያለፈው እ.ኤ.አ በ1773 ዓ.ም እንደሆነ የሚገልፁ ሰዎች ቢኖሩም፤ በታሪክ መዛግብት ውስጥ ለመጨረሻ ጊዜ በአካል የታየችውም፤ ጀምስ ብሩስ ኢትዮጵያን ለቅቆ ለመውጣት በሚዘጋጅበት ወቅት እ.ኤ.አ በዲሰምበር 1771 ዓ.ም የጎበኛት ጊዜ ነው::

ዛሬ በጎንደር ለምናያቸው የሥነ ሕንፃ ቅርሶች፣ የምንትዋብ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው:: በስልጣን ዘመኗ፣ በርካታ ህንፃዎች በጎንደር እንዲገነቡ አድርጋለች፤ ከእነዚህም መካከል የምንትዋብ ቤተመንግስት የሚባለው የራሷ ቤተመንግስትና ትልቅ ግብር መጣያ (የመመገቢያ) አዳራሽ ይጠቀሳሉ:: በቁስቋም፤ ለድንግል ማርያም መታሰቢያነት ከተሰሩት የደብረ ፀሐይ እና የንርጋ ስላሴ ቤተክርስትያኖች በተጨማሪ እዚያው እንደ መኖሪያ የተጠቀመችበትን ቤተመንግስት አስገንብታለች:: በያኔው የጎንደር ነገስታት ዘመን ዘይቤ ተገንብተው እስከዛሬ የዘለቁት ሕንፃዎች፤ በምንትዋብ መሪነት የተሰሩት ግንባታዎች መንፈስን የሚያድስ ማራኪ ውበት እንደነበራቸው ይመሰክራሉ::

ምንም እንኳ ስህተቶችን ብትፈፅምም፤ እቴጌ ምንትዋብ ከብዙዎች ልቃ ለረዥም አመታት ስልጣን ላይ የቆየች ጠንካራ መሪ ነበረች:: የ18ኛው ክፍለዘመን ሴት ብትሆንም፤ ለአርባ አመታት ያህል አገሪቱን ከመምራት አላገዳትም:: ስኮትላንዳዊው ተጓዥ የምንትዋብን የወጣትነት እድሜ ለመግለፅ ባሰፈረው ፅሁፍ፤ እውነትም “ሲበዛ የተዋበች፣ ጨዋ፣ የተረጋጋች፣ ተጫዋች፣ እንዲሁም ከእድሜዋ በላይ ትልቅ አዋቂና ብልህ” ነች ብሏል:: ሴት መሪዎች ባልነበሩትና ወንዶች የገነኑበት ዘመን ውስጥ የኖረች ሴት ነች፤ ግን ደፋር፣ ቆርጠኛና ጥበበኛ ሴት!

የመረጃ ምንጭ:- HTTP://ETHIOPIANWOMENUNLEASHED.ORG/?P=101

# ዶ/ር ሞሚና መሐመድ

የተወለድኩት ባህርዳር አቅራቢያ በምትገኝ ዘጌ በምትባል ትንሽ መንደር ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴንም ያጠናቀቅሁት በዚች ቦታ ነው:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ከቤተሰቦቼ ጋር ወደ ባህርዳር ከተዛወርን ብኋላ በባህርዳር መከታተል ችያለሁ:: የህክምና ትምህርቴን በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ክፍል ጨርሼ፤ የድህረ ምረቃ ስፔሻላይዜሽን ትምህርቴን በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ መከታተል ችያለሁ::

አብዛኛውን የልጅነት እድሜዬን ያሳለፍኩት በአባቴ ሱቅ ውስጥ በማገልገል ነው:: የመጫወቻ ጊዜ በጭራሽ የሌለኝ ሲሆን በአብዛኞቹ የልጆች ጨዋታዎች በቂ እውቀትና ችሎታ ስሌለኝ አብረውኝ የሚጫወቱ ልጆችንም በብዛት አላስታውስም:: ለቤተሰቦቼ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኔ መጠን በርካታ የቤተሰብ ኃላፊነቶችን የምይዘው እኔ ነበርኩ:: የትምህርት ህይወቴን የማሳልፈው በማጥናት ሲሆን ጎን ለጎንም በአባቴ ሱቅ ውስጥ ማገልግና ማዳራሳ (በመስኪድ የሚደረግ ኃይማኖታዊ አስተምሮ) ከማድረግ ባለፈ የቤት ውስጥ ወጪዎችን የማደላደል ኃላፊነት ነበረብኝ::

በሚያሳዝን ሁኔታ ገና ከህክምና ትምህርት ክፍል እንደተመረቅሁ አባቴን በሞት አጣሁ:: የአባቴ መሞት ታናናሾቼን የመንከባከብና እናቴን የመርዳት ኃላፊነት በእኔ ላይ ተጣለ:: እነዚህ ወቅቶች በህይወቴ ውስጥ በጣም ፈታኝ የነበሩ ጊዜያት ነበሩ:: በልጅነት እድሜዬም ይሁን ከዛ ብኃላ የገጠሙኝ በርካታ መሰናክሎችና ተግዳሮቶች ዛሬ ላለሁበት ደረጃ ለመድረስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገውልኛል:: በልጅነት እድሜዬ ባሳለፍኳቸው በርካታ ሁኔታዎች ምክንያት ጽናትንና ማኛውንም ነገር መቋቋም መቻልን የባህሪዬ እንደ አንዱ አካል እነዲሆን እንዳስቻለኝ አምናለሁ፤ በዛ ምክንያት የሚያጋጥሙኝን በርካታ መሳናክሎች ተቋቁሜ ወደፊት መጓዝን፣ ድጋሜ ማንሰራራትና በእምነት ያለምኩበት ግብ/ቦታ ላይ



መድረስ ችያለሁ::

“በህይወታችን ውስጥ የተለያዩ እድሎች እንዳሉና አንዳችን ከሌላኛው የተለየን እንደሆንን አምናለሁ፣

አንዳችንን ከሌላኛችን የሚለየን ያገኘነውን እድል አለመጠቀማችን ብሎም የተሻለ ነገር አለማለማችን ብሎም ህልማችንን ለማሳካት ጠንክረን አለመስራታችን ስለሆነ ለግባችን ስኬት ጠንክረን መስራ አለብን ብዬ አምናለሁ፡፡”

የህክምና ተማሪ እንደመሆኔ መጠን የኩላሊት ህመም ህክምና በተገቢው ሁኔታ አለመታከሙ ለሞት ሲዳርግ አይቻለሁ/ አስታውሳለሁ፡፡ በወቅቱ ምንም አይነት የኩላሊት ህክምናና እንክብካቤ የሚሰጥበት ማዕከል ባለመኖሩ የሙያዬ አንዱ አካል ለማድረግና በሙያው ላይ እስፔሻላይዝድ ለማድረግ አላሰብኩም ነበር፡ ፡ በኩላት እጥበት ህክምና ፈር ቀዳጅ በሆነው የቤቴል ቲቺንግ ጠቅላላ ሆስፒታል የውስጥ ደዌ ህክምና እስፔሻሊስት ሆኜ ከተቀላቀልኩ ብኃላና በበርካታ መድረኮች ላይ በመገኘት የኩላሊት ህክምና ላይ ያገኘሁት መረጃ ወደፊት ጥናቴና በኩላሊት ህመም ላይ እፔሻላይዝድ አድርጌ እንድሰራ ፍላጎቴን አነሳሳው፡፡ በኩላሊት ህመም የሚሰቃዩ ታካሚዎችን ምንም የመዳን ተስፋ እንደሌላቸው መመልከት መታገስ የምችለው ጉዳይ አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን በኩላሊት ህመም ህክምና ላይ የሚደርገው ጉዞ ቀላል ባይሆንም የሚያጋጥመኝ ፈተና ምንም ይሁን ምንም ምርጫዬ የሆነው ትምርቱን በተፈለገው ደረጃ መማር ነበር፡ ፡ ይህም አቅሜን ስለማውቀውና የተማርኩትንም ትምህርት ወደ ሀገሬ ኢትዮጵያ በመውሰድ በተግባር ላይ እንደማውለውም ስለማውቅ ነው፡፡ ተስፋ ወይም ፍላጎት ብቻ ሳይሆን፤ እነደዚህ አይነት ትምህርት ተምሬ የሀገሬን ዜጎችም የማገልገል ግዴታና እንዲህ ያለውን አገልግሎት ለማቅረብ ከሚያስፈልጉ ሰዎች መካከል እንደ አንዷ እነደሆንኩ አድርጌ እራሴንም ስለምቆጥር ነው፡፡



ሳይማሩ ካስተማሩኝ ወላጆቼ ከኢትዮጵያ ገጠራማ ስፍራ የተገኘሁ ሴት ሀኪም በመሆኔና እስካሁን ድረስ ላደረኩት የህይወት ጉዞና ባስመዘገብኳቸው አመርቂ ውጤቶች እኮራለሁ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የኩላት እጥበትና ንቅለ ተከላ የሚያደርግ ብቸኛው ብሎም በወቅቱ ከሚመጡ 70% በላይ ለሚሆኑ ታካሚዎች ከክፍያ ነፃ የሆነና አጠቃላይ ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት የሚችል ብቸኛው የመንግስት ማዕከል በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ ውስጥ የኩላሊት ንቅለ ተከላ የሚያደርግና የእጥበት አገልግሎት የሚሰጥ ማዕከል በማቋቋማችን በጣም እኮራለሁ፤ በተጨማሪም በሀገር ውስጥና ከውጪ ከመጡ የስራ ባለደረቦቼ ጋር በጋራ በመሆን በኢትዮጵያ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳካ የኩላሊት ንቅለ ተካላ በማድረጌና ማዕከሉን በማስተዋወቄ ከፍተኛ የደስታ ስሜት ይሰማኛል፣ ከፕሮግራሙ መጀመሪያ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የፕሮግራሙ ሚዲካል ዳይሬክተር በመሆን እያገለገልኩ እገኛለሁ፡ ፡ ከኩላሊት ንቅለ ተከላው ጎን ለጎን በርካታ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን የሚጨምሩ አዳዲስ ስራዎችን ማስተዋወቅ ችለናል፡፡

የኩላሊት ህመምን የሚያክሙና የሚንከባከቡ የህክምና ሰፔሻሊስት፣ የኩላሊለት እጥበት ነርስ፣ የኩላሊት ንቅለ ተከላ ነርስ፣ በኩላሊት በሽታ ላይ ጥናት የሚሰሩ የሰለጠኑ ባለሙያዎችና ሌሎች በርካታ ቁጥር ያላቸው ባለሙያዎች በመፈጠራቸው እኮራለሁ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የጤና አገልግሎት መስጫዎች ከጥራትና ከአቅርቦት ባሻገር ለታካሚዎች የሚፈልጉትን የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ተሚጋች ነኝ፡ ፡ ወጣት የህክምና ባለሙያዎችን ማማከርና ማስልጠን ያስደስተኛል፡፡ ምንም እንኳን የምሰራው ስራ ፈታኝ ቢሆንም ስራዬን እወደዋለሁ/ ያስደስተኛል፡፡ የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የኩላሊት ንቅለ ተከላ ማድረግ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሺዎች የሚቆጠሩ ስር የሰደደ የኩላሊት ህመም ያለባቸውን ታካሚዎችን ማከም የተቻለ ሲሆን ሁሉማ ማለት በሚያስችል ሁኔታ ማገገም ችለዋል፡ ፡ በርካታ ኩላሊታቸው ስራ ያቆመና የኩላሊት ንቅለ ተከላ የሚስፈልጋቸው የተለዩ ታካሚዎች የኩላሊት እጥበት እየተደረገላቸው ሲሆን ሌሎች ለኩላሊት ንቅለ ተከላው ተራቸውን በመጠባበቅ ላይ ይኛሉ፡ ፡ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ44 ጊዜ በላይ የኩላሊት ንቅለ ተከላ የተደረገ ሲሆን ከ95% በላይ የተሳካ ነበር፡፡

“በህይወቴ ውስጥ ትልቁ ግብ የሆነው ታካሚዎች የሚፈልጉትን ህክምና የማግኘትና የመገልግል መብት ያላቸው መሆኑን ማመንና ይህን እንዲገነዘቡ በማድረግ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡”

በኢትዮጵያ ውስጥ በቂ የሕክምና መገልገያዎች እና የሕክምና ባለሙያዎች ባለመኖራቸው መሰረታዊ



የ ህ ክ ም ና አገልግሎት ሳያገኙ የሚቀሩ ታካሚዎች እ ን ዳ ይ ኖ ሩ ና እጅግ የዘመኑ የጤና አገልግሎት መ ስ ጫ ዎ ች ያሏት ኢትዮጵያ እ ን ድ ት ፈ ጠ ር አልማለሁ። የተሻለ ትምህርት የሚሰጥባቸው ተቋማቶች የሚኖሩበት፣ ለወጣት የህክምና ትምህርት ተከታታዮች አግልግሎት የሚሰጡ በርካታ አሰልጣኞች/ አማካሪዎች ያሉባትን ኢትዮጵያ እንድትኖር እፈልጋለሁ። እንደ ጤና ባለሙያነቴ በዚህ መስክ ውስጥ ለሚገኙና ለሚሰሩ ሰዎች እንደ አንድ አርአያ እንደሆንኩ አመናለሁ። እኔ እንዳደረኩት ሁሉ ሌሎች መሰል ባለድርሻ አካላትም ሁሉን ነገር በአንድ መሰል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት የተሻለና ጥራት ያለው አገልገሎት መስጠት የሚያስችል ሲሆን በተለይ ያለው ሀብት በርካታ የኢትዮጵያ ዜጎችን ለማዳረስ ውስን በሆነበት ወቅት በጋራ ተባብሮ መስራት ትልቅ ለውጥ ማምጣት እነደሚያስችል እኔ ያደረኩትን ነገር እንደማሳያ ነው ብዬ አመናለሁ። የአገልግሎት እጥረት በተለይም የኩላሊት ህመም ህክምና አስመልክቶ ተደራሽ አቅርቦት መፍጠር መቻሉ ዋነኛጥ ቅ ሙ የኩላሊት ህምም ያለባቸው ወገኖች፣ ለተጠቃሚዎች ብሎም ለሀገር እጅግ ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ። እኔን ለወደፊቱ ትተካኛለች ብዬ በማሰብ አንዲት ብቁና ታታሪ የሆነች ሴት ሃኪም የኛን ክፍተኛ የኩላሊት ህክምና ስፔሻሊስት ትምህርት ስልጠና እ ን ድ ታ ደ ር ግ የመለመልኳትና ት ም ህ ር ቷ ን



እየተከታተለች ሲሆን እኔም ይህችን ልጅ የኔ ምትክ ለማድረግ በሙያዬና በምችለው መጠን እያገዝኳት እገኛለሁ። በአሁኑ ጊዜ በርካታ በኩላሊት ህክማና ላይ እስፔሻላይዝድ ለማድረግ የሚፈልጉ ሴት የህክምና ትምህርት ተከታታዮችና ዶክተሮች ትምህርት መርሃ ግብሩን ለመከታተል እየተጠባበቁ ይገኛሉ።

አንዲት ሴት ውጤታማ እንድትሆን ከሚያስፈልጓት ነገሮች መካከል ዋነኛው የትምርትና ሌሎች መሰል ድጋፎች ናቸው ብዬ አምናለሁ። ሴቶች ሁልጊዜ እርስ በእርስ መደጋገፍና መረዳዳት አለብን። በተለይም በትምህርታችንም ገፍተን መሄድ ይኖርብናል። አርአያ ሊሆኑን የሚችሉ ሴቶችን እንደ አንድ ስልት በመጠቀም ለመነቃቃትና የምንፈልገው ቦታ ለመድረስ መጠቀም አለብን። ያሉኝን የህይወት ልምዶች፣ ስኬቶችንና የገጠሙኝን ተግዳሮቶች በማካፈል ለሴት ተማሪዎቼ አመለካከትንና እሴቶችን ለማስተማር እጥራለሁ።

እንደ አምሳለና ሌሎች ስመ ጥር ሴቶችን ከማፍራትና ከማበረታታት ባለፈ በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ኢትዮጵያ የተጀመረው የለውጥ ጉዞ ላይ በርካታ ሴቶች እየተሳፈሩ ሲሆን ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ ሴት ፖለቲከኞቻችን የሀገሪቱን የፖለቲካና የአስተዳድር ምህዳር በመረከብ በተገቢው ሁኔታ እየሰሩ ይገኛሉ።

ሴቶች ወደ ኃላፊነት ሲመጡና ብቃት፣ ክህሎትና እውቀታችውን አውጥተው በስራ ላይ ሲያውሉ እልፍ አእላፍ እድገቶችን፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ መሻለሻሎችን እንደ ሀገር፣ እንደ ህዝብ በጋራ ሰርቶ በጋራ ለማደግ የሚኖረው የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው። እንደሚታወቀው ከዘጠኝ ወር ወዲህ ሴቶች ባለተለመዱ መልኩ የሀገሪቷን ከፍተኛ ኃላፊነቶችን ተረክበው ጉል ውጤቶችን እያስመዘገቡ ሲሆን በተለይም ከዚህ በፊት ባልተለመዱ የሚኒስቴርነትና የሀገሪቷን ርዕሰብሔር ቦታዎችን ጨምሮ ሴቶች እየተሾሙና ዕድል እየተሰጣቸው መሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው። ይህም ሀገሪቱ የያዘችውን የትራንስፎርሜሽን ጉዞ ከግብ ለማድረስ ሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤት ብቃት፣ ክህሎት፣ ልምድና ዕውቀት ያላቸውን ሴቶችን ወደ ኃላፊነት ከማምጣት ባሻገር አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል በማድረግ የሚፈለገውን ለውጥ ማስመዝገብ ያስችላል።

**"የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት!"**

የመረጃ ምንጮች:- http://ethiopianwomenunleashed.org/?p=69
:-https://www.awib.org.et/home/item/1101-momina-mohammed.html

# እንግዶቻችን

አዘጋጅ፡- አቤል ሞሴ

እንደሚታወቀው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለየ መልኩ በርካታ የሰው ኃይል የያዘና በርካታ ስራዎችንም እያሰራ የሚገኝ መስሪያ ቤት ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዚህ መስሪያ ቤት ከተቀጠሩ ጀምሮ ከ30 አመት በላይ የስራ ልምድ ያስቆጠሩ ብዙ አንጋፋ ሴት ሰራተኞች ይገኛሉ፡፡ በዚህ አምድ ስር ለዛሬ ሶስት በሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ውስጥ ለበርካታ አመታት ያገለገሉና አንቱታን ያተረፉ ሰራተኞችን የህይወት ተሞክሮ የምንቃኝበት ሲሆን ከእንግዶቻችን ጋር መልካም ቆይታ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን፡፡

በቅድሚያም ከእናቶችና ህፃናት ጤና ዳይሬክቶሬት በጸሃፊነት እየሰሩ ከሚገኙት **ቆይታ ከወ/ሮ ላቀች ሙላቱ ጎንጥ** ጋር አድረገናል ተከታተሉን፡፡



- ጤናችን፡- በመጀመሪያ ይህን መጠይቅ እንድናደርግ ፈቃደኛ ስለሆኑና በዚህች መፅሄትም ለሌሎች ወጣት ሴቶች የህይወት ልምዶትን ለማካፈል ስለፈቀዱ እናመሰግናለን፡፡ አንቱ ወይስ አንቺ ብዬ ልጥራ?
- ወ/ሮ ላቀች፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡ ችግር የለውም አንች እያልክ ብትጠራኝ አልቀየምም፡፡
- ጤናችን፡- መጀመሪያ ወደ ጤና ጥበቃ እንዴት ገባሽ?
- ወ/ሮ ላቀች፡- ገና በልጅነት እድሜዬ ነው ወደዚህ የገባሁት፡፡ እ.......... እንዴት ወደኋላ መለስከኝ መሰለህ (ሳቅ)፡፡ ወደ ጥያቄህ ስገባ ወደዚህ የገባሁት 12ኛ ክፍልን እንደጨረስኩ ያኔ የታይፕ ሙያ ስልጠና ስለነበር የአንድ አመት ትምህርት ተምሬ እንዳጠናቀቅሁ ማስታወቂያው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወጥቶ ያኔ ቅጥር የሚፈፀመው ህዝባዊ ኑሮ እድገት ያሁኑ የሲቪል ሰርቪስ በሚባለው መስሪያ ቤት በኩል ስለነበር ተወዳድሬ ሚኒስትር ቢሮ በረዳት ፀሃፊነት በ1972 ዓ.ም ተቀጠርኩ፡፡
- ጤናችን፡- በምን የስራ መስክ ነበር ስራ የጀመርሽው?
- ወ/ሮ ላቀች፡- ቅድም እንደነገርኩህ የተመረቅሁት በታይፕ ፀሀፊነት ስለነበር መጀመሪያም ስራ የጀመርኩት እዚህ መስሪያ ቤት በረዳት ፀሀፊነት ነበር፡፡
- ጤናችን፡- የስራ ቆይታሽ ምን ይመስል ነበር?
- ወ/ሮ ላቀች፡- ቆይታዬ ጥሩ ነበር፡፡ልጅነቴን የጨረስኩበት፣ የተማርኩበት ያደግሁበትና ብዙ ልምድ ያገኘሁበት በቃ ሁለተኛ ቤተሰቤ በለው፡፡ ከብዙ ዳይሬክቶሬቶች፣ ከብዙ ሃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ሀኪሞች ጋር በመስራቴ ብዙ ልምድ አግኝ ቼ በታለሁ፡፡ ሁሉንም እንዳልዘረዝርልህ ይከብዳል እንዳው ለምሳሌ በድሮ ስማቸው ነው የምነግርህ ፕላንና ፕሮግራም መምሪያ፣ ፖሊሲና ፋይናንስ ጀኔራል ዳይሬክቶሬት ቢሮ፣ ሚኒስትር ቢሮ እና የመሳሰሉት የስራ ክፍሎች ውስጥ ሰርቻለሁ፡፡
- ጤናችን፡- ይህን ያህል ብዙ አመት የመቆየቱ ሚስጥር ምንድነው?
- ወ/ሮ ላቀች፡- ሚስጥሩ.... እንግዲህ ሌላ ስላላየሁ ይሆናል (ሳቅ) ፡፡አብሬ ከምሰራቸው ሰዎች ጋር ሳልቀያየም ተከባብሬ ስለምሰራና ስለማልጋጭ ስራውንም ስለምወደው ይመስለኛል፡፡ እዚህ የነበሩ ሰዎች ጥሩ ስለነበሩ ሌላ ቦታ ለመሄድ አስቤ አላውቅም፡፡ ካደግሁበት ቤት የት እሄዳለሁ ብለህ ነው;(ሳቅ)፡፡
- ጤናችን፡- በቆይታሽ በትምህርት፣ በስራ ውጤታማነት እና የመሳሰሉት ያሳካሻቸው ስኬቶች ምንድናቸው?
- ወ/ሮ ላቀች፡-እዚህ ማደጌ ራሱ ስኬት ነው፡፡ ስኬቶቼ ብዙ ናቸው፡፡ እንደነገርኩህ የታይፕ ሙያ ከተማርሁ በኋላ እዚህ እየሰራሁ በአካውንቲንግ ከተፈሪ መኮንን ቴክኒክና ሙያ አሁን እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ የሚባለው ዲፕሎማ የ3 አመት ትምህርት ተምሬ ተመርቄአለሁ፡፡ ትምህርቱ ከሴክሬታሪ ጋር ተቀራራቢ ስለነበር እና ሙያውንም ስለምወደው እንዲሁም በመስሪያ ቤቱ የተለያዩ ስልጠናዎች ስለወሰድሁ በፀሀፊነት ስራዬ ቀጠልኩ፡፡ ተቋሙ ባዘጋጃቸው የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎች ለምሳሌ እንደ ወርድ ፕሮሰሲን የሚባል የኮምፒውተር ትምህርት ተምሬም ዲፕሎማ ተሰጥቶኛል፡፡
- ጤናችን፡- በስራ አለም ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ ያጋጠመሽ ገጠመኝ እና ያለፍሽበት መንገድ ሌሎችን የሚያስተምር ከሆነ ብታጫውችን?
- ወ/ሮ ላቀች፡- ስራን ተግባብቼ ስለምሰራ ይህን ያክል አስቸጋሪ የሆነ ገጠመኝ አላጋጠመኛም፡፡
- ጤናችን፡- ስለ ቤተስብ ህይወትሽ እስኪ አጫውችን?
- ወ/ሮ ላቀች፡- የምኖረው እንደ ልጆቼ ከማያቸውና ካሳደግኋቸው 2 ከወንድሜና ከእህቴ ልጆች ጋር ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲ እያስተማርኳቸው ጥሩ ደረጃ እየደረሱልኝ ነው፡፡ አንደኛዋ የኢንጅነሪንግ ተማሪ ስትሆን ሌላኛዋ ደግሞ የአካውንቲንግ ተማሪ ናት፡፡
- ጤናችን፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጊው

ነገር ካለ?

• ወ/ሮ ላቀች፡- በተለይ ለወጣቱ የማስተላልፈው በስራ ላይ ታጋሽነት፣ ቻይነት፣ አስተዋይነት በህይወታችን ወሳኝ የስኬት መንገዶች ስለሆኑ ልናዳብራቸው ይገባል፡፡ የሰው ልጅ ፀባይ የተለያየ ነው፡፡ እንደየፀባዩ ታጋሽ በመሆን በስራ ላይ ልምድ እየወሰድን አብሮ መስራት ያስፈልጋል፡ ፡ በተቻለ መጠን ኑሮ ቢከብድም ሁሌም መማር ራሳችንን ማሳደግ አለብን፡፡ አሁን ብዙ እድሎች አሉ፡፡

ለተቋሙም የማስተላልፈው መልእክት ሰራተኞችን የበለጠ ለማነሳሳትና ቆይታቸውን በዚሁ ተረጋግተው እንዲቆዩና በስራቸው ላይም ውጤታማ እንዲሆኑ የተለያዩ ማበረታቻዎችን ማድረግ የሚያስችል ስርዓት ቢዘረጋ እላለሁ፡፡ በመጨረሻም እናንተም እንዲህ አስታውሳችሁ ህይወቴን ወደኋላ መለስ ብዬ እንዳይ እና ይህን እድልም ስለሰጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

• ጤናችን፡-እኛም ጊዜሽን መስዋዕት አድርገሽ የህይወት ተሞክሮሽን ስላካፈልሽን በሚኒስቴር ምስሪያ ቤቱና በሴ/ህ/ወ/ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ስም እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ መልካም የስራ ዘመን ይሁንልሽ፡፡

## ቆይታ ከወ/ሮ አፀደ ብርሃኔ ተክሌ

ሁለተኛዋ እንግዳችንም በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ በሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት ኤክስኪዩቲቭ ሴክሬታሪነት በትጋት እያገለገሉ ያሉና ሌሎች ሴት ሰራተኞች ከሳቸው ይማራሉ ብለን በማሰብ እንግዳችን አድርገናቸዋል እንደተለመደው ከእኛ ጋር እንድትቆዩ በአክብሮት እንጋብዛለን ምልካም ንባብ፡፡



• ጤናችን፡- በመጀመሪያ ይህን መጠይቅ እንድናደርግ ፈቃደኛ ስለሆኑና በዚህች መፅሄትም ለሌሎች ወጣት ሴቶች የህይወት ልምዶትን ለማካፈል ስለፈቀዱ እናመሰግናለን፡፡ አንቱ ወይስ አንቺ ብዬ ልጥራ?

• ወ/ሮ አፀደ፡- እኔም እድሉ ስለተሰጠኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ችግር የለውም አንቺ በለኝ፡፡

• ጤናችን፡- እሺ አመሰግናለሁ፡፡ በመጀመሪያ ወደ ጤና ጥበቃ እንዴት ገባሽ?

• ወ/ሮ አፀደ፡- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወጥቶ ያኔ ቅጥር የሚፈፀመው ህዝባዊ ኑሮ እድገት ባሁኑ ሲቪል ሰርቢስ የሚባለው ማለትነው ያኔ ደብረ ታቦር ሆስፒታል በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር ስለሚተዳደር ለሆስፒታሉ የፀሃፊነት ሙያ በማውጣቱ ተወዳድሬ ነበር የገባሁት፡፡ በ1972 ዓ.ም ነው ስራ የጀመርኩት፡፡ ውይ ጊዜው………… እንዴት ይሮጣል? (ሳቅ) በ1977 ዓ.ም ከደብረ ታቦር ሆስፒታል በዝውውር ወደ ጤና ሚኒስቴር መጣሁ፡፡

• ጤናችን፡- በምን የስራ መስክ ነበር ስራ የጀመርሽው?

• ወ/ሮ አፀደ፡- በታይፒስትነት ነበር፡፡

• ጤናችን፡- የስራ ቆይታሽ ምን ይመስል ነበር?

• ወ/ሮ አፀደ፡- በ1977 ዓ.ም ከደብረ ታቦር ሆስፒታል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በዝውውር ስመጣ የተመደብኩት በንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ነበር፡፡ በዚሁ ቢሮ 8 ወር ከሠራ ሁብኋላ በ1978 ዓ.ም ጅማ ጤና ሣይንስ ኢንስቲትዩት በዕድገት ሄድኩኝ፡፡ ጅማ ጤና ሣይንስ ኢንስቲትዩት 4 ዓመት ከ4 ወር ከሠራሁ በኋላ በ1982 ዓ.ም ወደ ጤና ጥበቃ ሚ/ር ኤድስ መ/መ/ፕሮግራም በዝውውር በመምጣት በሙያዬ ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ የምክትል ሚኒስትር ፀሐፊ ሆኜ እንድሠራ ከመ/ቤቱ በደረሰኝ የጽሑፍ ትዕዛዝ መሠረት ሳገለግል ቆይቼ በወቅቱ በነበረው አዲስ የሥራ ድልድል በ1986 ዓ.ም ፖሊሲና ፕላን ዳይሬክቶሬት ተመድቤ 6 ዓመት እንዳገለገልኩ በ1992 ዓ.ም ለቤተሰብ ጤና ክብካቤ መምሪያ በወጣው የውስጥ ዕድገት ማስታወቂያ ተወዳድሬ ባገኘሁት ውጤት መሠረት በመምሪያው 1 ዓመት አካባቢ ከሠራሁ በኋላ በ1993 ዓ.ም በራሴ ጥያቄ ወደ በሽታዎች መ/መ/መምሪያ ተዛውሬ 8 ዓመት አገልግያለሁ፡፡ ከዚህም በኋላ እንደገና በነበረው የመ/ቤቱ የመዋቅር ለውጥ በ2001 ዓ.ም ሜዲካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት እንድሠራ ተመድቤ ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ በ2003 ዓ.ም የሚኒስቴር መ/ቤታችን ፀሐፊዎች በሙሉ ኮሜርስ ሄደን እንድንፈተን በተወሰነው መሠረት ባገኘሁት የፈተና ውጤት ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት /ፕሮግራም ዘርፍ /በExecutive II ደረጃ ተመድቤ ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ በ2005 ዓ.ም ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት /ኦፐሬሽን ዘርፍ/ ተዛውሬ እስከ መስከረም ወር 2011 እያገለገልኩ እያለሁ የኦፐሬሽን ዘርፍ በሚ/ር ዴኤታ መመሪያ በመቅረቱ ከጥቅምት 28/2011 ጀምሮ በሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት / ሪፎርምና አስተዳደር ዘርፍ/ ተዛውሬ በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡ ቆይታዬ ይህን ይመስላል፡፡

• ጤናችን፡- ይህን ያህል ብዙ አመት የመቆየቱ

ሚስጥር ምንድነው?

•ወ/ሮ አፀደ፡- ሥራ የጀመርኩት በልጅነት ጊዜዬ ገና ሃያ ዓመት ሳይሞላኝ በመሆኑና በጤና ጥበቃ ሥር በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ማለትም በሆስፒታል፣ በጤና ረዳት ት/ቤት፣ በጅማ ጤና ሣይንስ ኢንስቲትዩት (ድሮ በጤና ጥበቃ ሥር ስለነበር) እንዲሁም በዚሁ በመ/ቤታችን በተለያዩ መምሪያዎች፣ ዳይሬክቶሬቶችና ጽ/ቤቶች በመሥራቴ ከእያንዳንዱ ክፍል ብዙ የሥራ ልምድ ስላገኘሁበትና ሌላ መ/ቤት ስለማላውቅ ይመስለኛል፡፡

•ጤናችን፡- በቆይታሽ በትምህርት፣ በስራ ውጤታማነት እና የመሳሰሉት ያሳካሻቸው ስኬቶች ምንድናቸው?

•ወ/ሮ አፀደ፡- ትምህርትን በተመለከተ ስቀጠር ከ9-12ኛ ክፍል በተማርኩት የቀለምና ንግድ ሥራ ትምህርት ባጠናቀቅኩበት ዲፕሎማ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ 10+2 የነበረኝ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ደግሞ የሲኦሲ ብቃት ማረጋገጫ ያለኝ፣ በLevel IV የተመረቅኩና ትምህርት ዕድሜ አይወስነውም በሚባለው መሠረት በአሁኑ ሰዓት ትምህርቴን በManagement ሙያ በዲግሪ እየተከታተልኩ የምገኝ ስሆን የሥራዬን ውጤታማነት ግን ማህደሬ ውስጥ የሚገኙትን ከተለያዩ የሠራሁባቸው ቢሮዎች የተፃፉልኝን የምሥጋና ደብዳቤዎች መመልከት የሚቻል መሆኑን እገልፃለሁ፡፡

•ጤናችን፡- በስራ አለም ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ ያጋጠመሽ ገጠመኝ እና ያለፍሽበት መንገድ ሌሎችን የሚያስተምር ከሆነ ብታጫውቺን?

•ወ/ሮ አፀደ፡- በሥራ ዓለም ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ የገጠመኝ ነገር የለም፡፡

•ጤናችን፡- ስለ ቤተሰብ ህይወትሽ እስኪ አጫውቺን?

•ወ/ሮ አፀደ፡- የቤተሰብ ሕይወቴ በተመለከተ ባለትዳርና የሁለት ወንድ ልጆች እናት ነኝ፡፡ የመጀመሪያው ልጄ በአሁኑ ዓመት በሕክምና ትምህርት ይመረቅልኛል ሁለተኛው ልጄ በአካውንቲንግ ሙያ የአንደኛ ዓመት የዲግሪ ተማሪ ነው፡፡ በቤተሰብ ሕይወቴ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡

•ጤናችን፡-በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጊው ነገር ካለ?

•ወ/ሮ አፀደ፡- ይህን ያህል ዓመት ስሠራ ካየሁት በመነሳት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡ ይኸውም ማንም ሰው ሥራ ሲቀጠር ማንም ሳያስገድደው አምኖበት ሥራውን ወዶ መሆኑን በመረዳት የተቀጠረበትን የሥራ መስክ መውደድና ማክበር አለበት፡፡ እንዲሁም የተሠማራበትን ሥራ በታማኝነትና በቅንነት መወጣት ግዴታውንና መብቱን ማወቅ፣ ሚስጥር መጠበቅ፣ የሚሠራበትን ክፍል እንደ መኖሪያ ቤቱ ማየት፣ ከሥራ ባልደረቦቹና ከአለቆቹ ጋር ተግባብቶ መሥራት እና በአጠቃላይ በሚሠራበት መ/ቤት የእኔነት ስሜት ከልብ ያደረበት መሆን እንደሚገባ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡ በመጨረሻም ለየት ባለመልኩ በዚህ መስሪያ ቤት ውስጥ ለረጅም ዓመት ያገለገሉ ሴት ሰራተኞችን አፈላልጋችሁና አስታውሳችሁ ቃለ መጠይቅ ስላደረጋችሁልኝና የመጽሔታችሁ እንግዳ ስላደረጋችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

•ጤናችን፡-እኛም ጊዜሽን መስዕት አድርገሽ የህይወት ተሞክሮሽን ስላካፈልሽን በሚኒስቴር ምስሪያ ቤቱና በሴ/ህ/ወ/ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ስም እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ መልካም የስራ ዘመን ይሁንልሽ፡፡

•ወ/ሮ አፀደ፡- አሜን ለእናንተም መልካም የስራ ዘመን፡፡

## ቆይታ ከወ/ሮ ማስተዋል ስንሻው ሰማኝ

ጋር አድርናል ተከታተሉን፡፡

ሶስተኛዋ እንግዳችንም በሚኒስቴር መስራያ ቤት ውስጥ በሰው ሀብት አስተዳድር ዳይሬክቶሬት የመዝገብ ቤት ኃላፊ በመሆን በትጋት እያገለገሉ ያሉና ሌሎች ሴት ሰራተኞች ከእሳቸው ይማራሉ ብለን በማሰብ እንግዳችን አድርገናቸዋል እንደተለመደው ከእኛ ጋር እንድትቆዩ በአክብሮት እንጋብዛለን መልካም ንባብ፡፡



•ጤናችን፡- በመጀመሪያ ይህን ቃለ መጠይቅ እንድናደርግ ፈቃደኛ ስለሆኑ እናመሰግናለን፡፡ እርሶ እያልኩ ልቀጥል? ወይንስ አንቺ? መካከል ላይ እንዳልሳሳት ብዬ ነው፡፡

•ወ/ሮ ማስተዋል፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡ ችግር የለውም አንች ብለህ አውራኝ፡፡

•ጤናችን፡- መጀመሪያ ወደ ጤና ጥበቃ እንዴት ገባሽ?

•ወ/ሮ ማስተዋል፡- የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ከትምህርት ቤት ስንወጣ ወባ መቆጣጠሪያ ድርጅት ማስታወቂያ ስላወጣ እንመዝገብ ስትለኝ በዚያዉ በመሄድ ተመዘገብንና ተወዳድረን አልፈን ስራ ጀመርን፡፡ ያኔ በጠቅላላ አገልግሎት ስራ ክፍል ነበር የተመደብኩት፡፡

•ጤናችን፡- የስራ ቆይታሽ ምን ይመስል ነበር?

•ወ/ሮ ማስተዋል፡- የስራ ቆይታዬ አባቴ በፍጹም ስራ እንድሰራ አይፈልግም ነበር፡፡ ትምህርቴን

እንድጨርስ ነበር ፍላጎቱ፡፡ ሆኖም በጓደኛዬ እና በእናቴ እገዛ ስራዉን ጀመርኩ፡፡ ስራዉን ስሰራ ፍጹም ደስተኛ ነበርኩ፡፡ ምክንያቱም የስራተኛዉ አክብሮት፣ ፍቅርና መግባባት በጣም ደስ ይል ነበር፡፡ ወባ መቆጣጠሪያ ድርጅት ለእኔ ብዙ ትምህርትና እዉቀት ያገኘሁበት ነዉ ማለት እችላለሁ፡፡ በወቅቱ ስራ የምሰራው ትምህርቴን እየተማርኩ ስለነበር የደረጃ እድገት አግኝቼ ወደ ጤና ጥበቃ ሚ/ር በአሁኑ መጠሪያ ስሙ ሪከርድና ማህደር ስራ አመራር አገልገሎት በደረጃ እድገት መጣሁ፡፡ የስራ ክፍሉ እጅግ በጣም ስራ የሚበዛበት ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡

- ጤናችን፡- ይህን ያህል ብዙ አመት የመቆየቱ ሚስጥር ምንድነው?
- ወ/ሮ ማስተዋል፡- ምንም ሚስጥር የለም፡፡ ስራዬን በጣም እወደዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ብዙ እዉቀት አግኝቼበታለሁ፡፡ ሌላው ትዳር በመመስረቴና ልጆች በመዉለዴ ልጆቼን በማሳደግና ጎን ለጎን ትምህርቴንም በመማር ላይ ስለነበርኩ ሌላ የመፈለጉ ወይም የመልቀቁ ሃሳብ አልነበረኝም፡፡ በዚሁ የምወደውን ስራ እየሰራሁ ቤተሰቦቼን እያስተዳደርኩ ትምህርቴንም እየተማርኩ ለውጥ ማምጣት እችላለሁ ብዬ ስላሰብኩም ጭምር ነበር፡፡
- ጤናችን፡- በቆይታሽ በትምህርት፣ በስራ ውጤታማነት እና የመሳሰሉት ያሳካሻቸው ስኬቶች ምንድናቸው?
- ወ/ሮ ማስተዋል ፡- በቆይታዬ አሳካሁ ብዬ የማስበዉ ጤና ጥበቃ ሚ/ር ሲመሰረት ጀምሮ ከ114ሺ በላይ የተከፈቱ የግለሰቦች ማህደር ነበር፡፡ አከፋፈቱም በፊደል ቅደም ተከተል ፋይል ቢከፈትም ባለጉዳይ ለማስተናገድ ያንን ሁሉ ማንበብ ይጠበቅብን ነበር፡፡ ሆኖም ይህንን በተመለከተ ለበላይ አካል በማቅረብና ማህደሮች እንዲደራጁ በታዘዘዉ መሰረት ልየታዉን ከስራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን የጤና ባለሙያዎችን ፣ የአስተዳደር ሰራተኞችን እና ሌሎችን ማህደር በመለየት የጤና ባለሙያዎችን የግል ማህደር ወደ ዳታ በማስገባት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን ይህም ለእኔም ለስራ ባልደረቦቼም ትልቅ ስኬት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡
- ጤናችን፡- በስራ አለም ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ ያጋጠመሽ ገጠመኝ እና ያለፍሽበት መንገድ ሌሎችን የሚያስተምር ከሆነ ብታጫውችን?
- ወ/ሮ ማስተዋል ፡- ካሉኝ ገጠመኞች ምን አልባት አስተማሪ ሊሆን ይችላል ብዬ የማስበዉ BPR ሲዘጋጅ በወቅቱ በጠቅላላ አገልግሎት ስር ነበር የተዋቀረው፡፡ ሆኖም ቀደም ሲል የተዘጋጀው የባለሙያዎችን መረጃዎችን በመረጃ ቋት ለማስገባት በተደጋጋሚ ለአጋር ድርጅቶች በደብዳቤ ይጠየቅልን፤ በጀትም ይያዝልን ብዬ ብጠይቅ ምንም ምላሽ ሊሰጡኝ አልቻሉም፡፡ እራስሽ መጠየቅ ትችያለሽ ሲሉኝ እኔ ምንስልጣን አለኝና ነው የውጭ ድርጅት የምጠይቃቸው ስላቸው እንደፈለግሽ አሉኝ፡፡ እጅግ በጣም አዘንኩ የግሌ አይደለም የተቋሙ ነዉ ምን ማድረግ አለብኝ ብዬ ማሰብ ጀመርኩ መጀመሪያ ወደ ድርጅቱ መሄድ አሰብኩ፤ በራሴ ትራንስፖርት ወደ ቱሌን ድርጅት ሄድኩ፤ ግቢዉ ውስጥ አንድም ሰራተኛ አልነበርም፡፡ አጋጣሚ አንድ ወጣት አገኘሁ እና እባክህ የድርጅቱን ኃላፊ ፈልጌ ነዉ ብትነግረኝ ስለዉ ለምን ፈለግሻቸዉ ሲለኝ ለስራ ጉዳይ ነዉ ስለዉ ወደ ቢሮ ገባን፡፡ እኔ አንተን አይደለም የምፈልገዉ ስራ አስኪያጁን ነው ስለዉ ለካንስ የአጋር ድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ነበሩ ስለማላቃቸው ዶ/ር እከሌ እባላለሁ ሲለኝ በስም አውቀው ስለነበር በጣም ነው የደነገጥሁት፡፡ ምክንያቱም የምጠብቀዉ በእድሜ ጠና ያለ ሰው ነውና፡፡ እሱ እጅግ በጣም ወጣት ነበር፡፡ ይቅርታ ጠይቄ የመጣሁበትን አላማ በግልፅ ነገርኩት፡፡ ምንም ችግር የለም ከመስሪያ ቤቱ ጋር ተዋውለን በቅርብ ቀን እንጀምራለን በርቺ ግፊበት እናግዝሻለን ብሎ አበረታትቶ ሸኘኝ፡፡ በዚህ ዙሪያ ብዙ ችግር ገጥሞኝ ነበር፡፡ ነገር ግን እስከ በላይ አካል በመሄድ ያለመሰልቸት ሊሳካ ችሏል፡፡
- ጤናችን፡- ስለቤተሰብ ህይወትሽ እስኪ አጫውችን?
- ወ/ሮ ማስተዋል፡- የቤተሰብ ህይወቴ ወላጆቼ ትዳር ከመሰረቱ ከረዥም ጊዜ በኋላ በአዲስ አበባ በቀድሞ ስሙ ደጃች ባልቻ አባነፍሶ ሠፈር የአሁኑ ስሙ አብነት ሰፈር ተወለድኩ፡፡ በተወለድኩ በ5 አመቴ አባቴ ለስራ ወደ ወለጋ ሆሮ ጉድሩ ሲሄድ አያቴ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር አትሄድም በማለት ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር ወሰደችን፡፡ እዚያዉ ስኖር ከ5 አመት በኋላ አባቴ ሊጠይቀኝ ሲመጣ ሲያየኝ እጅግ በጣም አዘነ ወዲያዉኑ ወደ ተወለድኩበት አዲስ አበባ አመጣኝ፡፡ ትምህርቴን ጀመርኩና በመማር ላይ እያለሁ ስራ ጀመርኩ፡፡ ትዳርም መስርቼ የ4 ወንድ ልጆች እናት ነኝ፡፡ ሁለቱ ልጆቼ ተምረው ተመርቀው ስራ ይዘውልኛል፡፡ ሁለቱ ኮሌጅና አንደኛ ደረጃ በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ በነገራችን ላይ አባቴን እጅግ እጅግ በጣም እወደዋለሁ ያለ እሱ ህይወት ያለኝ አይመስለኝም ነበር ነፍሱን ይማረውእና፡፡
- ጤናችን፡-በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጊው መልዕክት ካለ?
- ወ/ሮ ማስተዋል፡- ማስተላለፍ የምፈልገዉ በዘር በሀይማኖት በጎሳ ሳንከፋፈል አንዲት ኢትዮጵያን በያለንበት ስራ ላይ ተግተን በመስራት እናልማትና እናሳድጋት፡፡

በመጨረሻም እናንተም እንዲህ አስታውሳችሁ ይህን እድልም ስለሰጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

- ጤናችን፡-እኛም ጊዜዎትን ሰጥተው የህይወት ተሞክሮዎን ስላካፈሉን በጣም እናመሰግናለን፡፡

# እናትነትና ሴትነት
# ሴትነትና እናትነት

አዘጋጅ፡- አቤል ሞሴ

## ‹‹ ለአንቺ_ጊዜ_ሲሆን...››

ሰማኒያ አንድ ቋንቋ፣ እግዜር እንዳልሰጠን
ለአንቺ ጊዜ ሲሆን፣
ምነው ቃል አጠረን?
የትክሻሽን መዛል፣
የተረከዝሽን
መቁሰል፧
የልብሽን ቋጠሮ
እምነት፣
የተስፋሽን ሰገነት፧
የፊትሽን ገፀ ንባብ፣
የጀርባሽን እሮሮ
ምን ቋንቋ
ይገልፀዋል፣ በስሜት
ምናብ ተሻግሮ?
ለካስ ‹ቃል›ም ውድ ነው፣ ለ ከሰመ ማንነት፣
ለእርባና ቢስ ኑሮ!
ግዴለም ይንጠፍ ሆሄ፣ ግዴለም ይንጠፍ ቃሉ፣
የፎቶውን ጥልቀት፣ ምስሉን አስተውሉ፣
እንዲህ ነው የሚገለፅ፣ ‹‹ሀገር››ን በሰው ሲስሉ!



(Zelalem T እነደፃፈው)

## እማ ሰላንቺማ

እማ መዳኒቴ ፣ እማ አንደበቴ፣ እማ የኔ ጥላ
እማ ያንቺ ህይወት በደስታ ይሞላ
አንቺ ካለሽ በቃ አልጠጣ አልብላ
እሰትንፋሴ እኮ ነሽ የኑሮዬ ደሰታ
ክፉ የመጣብሽ ቀን ያርገኝ ባንቺ ቦታ
ሳትርቂ ከጎኔ ሳለቅሰ እያነባሽ
በሄድሽበት ሁሉ
አዝለሽኝ በጀርባሽ
ለቅሶ ቤት በጀርባሽ
ሰርግ ቤት በጀርባሽ
ዳገቱን >> >>ሽ
ቁልቁለት >> >>ሽ
ዝናብን >> >>ሽ
ፀሐይን >> >>ሽ
እማምዬ እናቴ ምን
ይሆን ሁለታሽ
በየትኛው ቃላት በምን
ይገለፃል
እማ ሰላንቺማ መች
ተነግሮ ያልቃል



ከወርቅነህ ይብጌታ

## ምጽአተ ማዕበል

እባክህ አምላኬ ዝናቡን አውርደው
ተሰነጣጠቀ ደረቀብኝ ማሳው ፥
ይለምናል ጌታን ምስኪኑ ገበሬው፧
ለከብቶቼ ግጦሽ ለልጆቼ ቆሎ፧
ለግብር መክፈያ ማሽላ በቆሎ፧
ፍጠን ድረስልኝ ዝናቡ ና ቶሎ ፥

ኤጭ ይሄ ዝናብ ተመልሶ መጣ፧
አርፌ ልቀመጥ ደጅም አያስወጣ፧
ጭቃ ብቻ ሆነ አያስኬድ መኪና፧
ይህ አሮጌ ሰፈር ያልረባ ጎዳና፧
ይላል ባለቪላው በረዳው ላይ ሆኖ
አፍንጫውን ሳይቀር በጋቢ ጀቡኖ

የዘንድሮው ዝናብ መነቸከ ባሰ፧
ጣራው አረግርጎ ግድግዳው ፈረሰ፥
እባክህ ዝናቡ ተው ውረድ በቅጡ፧
አትጨክን በድሃ አትሁንብን ቁጡ፧
ትላለች በብሶት ጠላ ሻጭዋ ደሃ፧
ድስት እየደቀነች ለፍሳሹ ውሃ፥

ዝናብም ልመና ይሰማል በቶሎ፧
ይመጣል በርዶ ነፋስን ቀላቅሎ፧
ነጎድጓድም ሳይቀርመብረቅ አስከትሎ፧
በደረቁ ምድር አጉረምርሞ አለፈ፧
ባረባው ጎዳና ሽክሙን አሳረፈ፧
ግድግዳ አፈረሰ ጣራውን ነቀለ፧
ለፈለገው ትቶ ላልፈለገው ጣለ፧

ሠፍራ መለየትስ በቀልቡ የታለ፧
ይህንን የሰማ ያየ ያስተዋለ፧
ጩኸት አስተጋባ እሮሮው ቀጠለ፧
አይ ዝናብ አይ ዝናብ ያንተ ሠራ እያለ _ _ _
ደራሲም ተነሳ ብዕሩን አሾለ፧
መከተቡን ያዘ ወረቀት ቆለለ፧
ርዕሱን ሲሰይም ማዕበል ነው አለ፡፡

ጌቱ ሀይሉ



# ስርዓተ ፆታና አካል ጉዳት

አዘጋጅ፡- ዘውዱ ጉሉማ

የአፍሪካውያን ባህሎች ባመዛኙ ለሴቶች አነስ ያለ አመለካከት እና ቦታ ይሰጣሉ፡፡ በተለይ ያለው የቤተሰብ ሀብት ውስን በሆነበት አጋጣሚ በተለይም የአካል ጉዳት ሰለባ የሆኑት ልጃገረዶች የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ይልቅ የድህነት ገፈት ቀማሽ ናቸው፡፡ በተለይም ሴት ልጅ መዳር እና ወደባሏ ቤተሰቦች መሄድ ነው ያለበት የሚል ግንዛቤ ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ፣ ለጋብቻ አይሆኑም/አይመጥኑም የሚባሉት አካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች ዋጋ እንደሌላቸው ይቆጠራሉ፡፡

የአካል ጉዳተኛ ሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ድርሻ (1%) ከአጠቃላዩ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች የትምህርት ተሳትፎ ድርሻ (3%) እጅግ በጣም ያነሰ ነው፡፡ የአካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች አጠቃላይ የትምህርት ተሳትፎ



በተለይም የሥራ ዕድል ለማግኘት የተሻለ እውቀት ክህሎት የሚገኝባቸው ትምህርት ዓይነቶች ያላቸው ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

ከጠቅላላ አካል ጉዳተኞች መካከል እንኳን የአካል ጉዳተኛ ሴቶች ሥራ የማግኘት እድል ከእጥፍ በላይ ያነሰ ነው፡፡ ይህም የአካል ጉዳተኛ ሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ማነስና የቀጣሪዎች/የአሠሪዎች የተሳሳተ እና አሉታዊ ግንዛቤ ምክንያት የተፈጠረ ነው፡፡ ሥራ የማግኘት እድላቸው አነስተኛ በመሆኑ፣ አካል ጉዳተኛ ሴቶች ከሌሎች አካል ጉዳት ከሌለባቸው ሰዎች እና አካል ጉዳተኛ ወንዶች እንኳን አንፃር ሲታይ የድህነት ሁኔታዎች እጅግ የባሰ ነው፡፡

የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች፣ በተለይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች ወሲዊ ፍላጎት የሌላቸው ወይም ወሲባዊ ፍላጎታቸው እጅግ የቀዘቀዘ እንደሆነ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ይህም ለራሣቸው ያላቸውን ግምት እና ዋጋ ዝቅ ያለ አድርገው እንዲመለከቱት ከማድረጉም ባሻገር ለወሲባዊ ጥቃት የተጋለጡ እና ደካማ ያደርጋቸዋል፡፡

አካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች ከወንድ መሰሎቻቸው በበለጠ ጥገኛ፣ የማይጠቅሙ፣ ታማሚ፣ እንደ ህፃን ሁሌ ክብካቤ የሚያስፈልጋቸው፣ እርዳታ ፈላጊ ተደርገው ስለሚወስዱ ትዳር የመመስረት ዕድላቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ዘግይተው ትዳር ቢመሰርቱም ጋብቻው ቶሎ የመፍረስ አጋጣሚው ሰፊ ይሆናል፡፡

እነደነሱ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ ሊወልዱ ይችላሉ በሚል ግምት ባመዛኙ ስነት ያለባቸው ሴቶች እንዲወልዱ አይፈለግም፡፡ አካል ጉዳተኛ ሴቶች ከአካል ጉዳተኛ ወንዶች ይበልጥ ያለማግባት፣ ቆይቶ የማግባት እና ቶሎ የመፍታት እድል አላቸው፡፡

## የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በጤናው ዘርፍ ማካተት

የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በጤናው ዘርፍ ማካተት ስንል አካል ጉዳተኞች ፍላጎቶቻቸውና መብቶቻቸው ሳይዘነጉና ወደ ጎን ሳይባሉ በእኩልነትና በፍትኃዊነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አካቶ ስነት/አካል ጉዳት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የተለዩ እርምጃዎችን በመውሰድ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ጉዳይ የትኩረት አቅጣጫ በማድረግ ልናሳካው የምንችለው ግብ ነው፡፡ ስነትን/እክልን ወይም አካል ጉዳትን የትኩረት አቅጣጫ ማድረግ በጤናው ዘርፍ የተያዙ ግቦችን ለማሳካት የምናደርገው ተከታታይ እንቅስቃሴ እና ሂደት ነው፡፡ ይህ ሂደት በሁሉም መስክ በታቀዱ ተግባሮች፣ ድንጋጌዎች ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች አተገባበር ወቅት በየደረጃው የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ጉዳይ እንድናተኩርበት ይረዳል፡፡



አካል ጉዳትን/ ስነትን የትኩረት አቅጣጫ ማድረግ አካቶ ስነት ለማሳካት አንድ ስትራቴጂ ነው፡፡ ይህ ተግባር በሁሉም ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ኘሮግራሞች ሲወጡ፣ ፖሊሲዎች ሲነደፉ እንዲሁም ተግባራዊ ሲደረጉ እና ክትትልና ግምገማ ሲደረግባቸው የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ጉዳይ ቸል እንዳይባል እና ትኩረት እንዲሰጠው ያግዛል፡፡ ስለዚህ ማካተት ማለት፤ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች በእኩል ደረጃ በጤናው ዘርፍ ፍትኃዊ ተጠቃሚነትንና ተደራሽነትን ማረጋገጫ እና መድልዎ



ሥር እንዳይሰድ መረጃ መንገድ ነው፡፡ የሴት አካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በጤናው ዘርፍ ለማሳካት ሳንካ ሊሆኑ የሚችሉ አበይት ምክንያቶች ስነት 'የትኩረት አቅጣጫ ማድረግ' እና/ወይም 'ኣካቶ ስነት' አካል ጉዳት ላይሳኩ የሚችሉበት አጋጣሚ፤ በርካታ ሲሆኑ ይህም ተቋማዊ ድጋፍ አለማግኘት/አለመኖር፣ ፖሊሲዎችን ማውረድ እና ግንዛቤ መፍጠር ሲያቅት/ሲጠፋ፣ ልማዳዊ የሆኑ ስነትን አስመልክቶ ያሉ አመለካከቶችን ለመለወጥ/መስበር ሳይቻል ሲቀር፣ ተግባራዊ የሆነ አቅጣጫ አመላካች ሁኔታ ሳይኖር ሲቀር፣ በቂ ሀብት/በጀት የሰለጠነ የሰው ኃይል ሳይመደብ ሲቀርና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችን መተግበር/ማካተት ሳንችል ሲቀር ነው፡፡

ምንጭ፡- ከሀንዲካፕ ኢንተርናሽና የአካል ጉዳተኝነት ማካተቻ ማኑዋል

# ስለአልቢኒዝም ምን ያህል ያውቃሉ

አዘጋጅ፡- ዘውዱ ጉሉማ

አልቢኒዝም ሰዎች በአካላቸው/በቆዳቸው ስር ይዘው መወለድ የሚገባቸውን የቀለም ንጥረ ነገር (pigment) እጥረት ወይም ከናካቴው ባለመኖሩ ከእናት ከአባታቸው የሚወርሱት ነው፡፡ ሰዎች፣ እንስሳት እና ተክሎች እንኳ በአልቢኒዝም ሊጠቁ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሰዎች በተፈጥሮ ከሚያገኙት የወላጆቻቸው መልክ የተለየ መልክን እንዲይዙ ያደርጋቸዋል፡፡ ሰውነታቸው መደበኛ የሆነ የሜላነን እጥረት/አለመኖር ሲያጋጥመው ዓይን፣ ቆዳ እና የፀጉር ቀለም በተለየ የነጣ ወይም ግራጫ መልክ እንዲይዝ ያደርገዋል፡፡



ከዓይን ችግር በስተቀር አብዛኛዎቹ አልቢኒዝም ያለባቸው ሰዎች ልክ እንደማንኛውም ሰው ጤናማ ናቸው፡፡ በጣም አልፎ አልፎ በአልቢኒዝም በተጨማሪ ሌሎች የጤና ችግሮችን ያካተተና በሰዎች ላይ የተለያየ የጤና እክል የሚፈጥር የአልቢኒዝም አይነት አለ፡፡

አልቢኒዝም ከሰው ወደ ሰው በንክኪ፣ በትንፋሽ ወይም በሌሎች መሰል ሁኔታዎች ተላላፊ አይደለም፡፡ ሰዎች የአልቢኒዝም የዘር ግንድ ወይም ጂን ካለባቸው ወላጆቻቸው ስለሚወርሱ በአልቢኒዝም ተጠቅተው የሚወለዱ ቢሆንም ወላጆች የሚወልዷቸው ልጆች ሁሉም በአልቢኒዝም ይያዛሉ ማለት ሳይሆን ከሚወልዷቸው አራት ልጆች በአማካይ አንዱ አልቢዝም ይኖርበታል፡፡ ቢሆንም አልቢኒዝም ያለበት ሰው ጤናማና ማንኛውንም ስራ መከወን የሚችል ነው፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ አልቢኒዝም ያለባቸው ሰዎች በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጪ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የሚኖሩ አልቢኒዝም ያለባቸው ሰዎች ግን ህይወታቸው የጭንቅ ህይወት እየሆነባቸውና ልጆቹ በሚኖርባቸው ማህበረሰብ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች አልቢኒዝም ያለባቸውን ልጆች እጆችና እግሮቻቸው እየተቆረጡ ይገኛል፡፡ ለዚህም እንደዋንኛ ምክንያት ተደርጎ




የሚወሰደው በተወሰኑ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ የአካል ክፍሎቻቸው አስማታዊ ኃይል እንዳላቸውና ተቆርጦ ለጠንቋይ ዶክተሮች ቢቀርብና ጥቅም ላይ ቢውሉ ሀብት፣ ኃይልንና ዘላቂ ጤናን ያመጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አልቢኒዝም ያለባቸው ሰዎች ለሰውነት ክፍሎቻቸው ሲባል አካላቸው በቁም በሰዎች እየተቆራረጠ ሲሆን እጆቻቸውና እግሮቻቸው በጥቁር ገበያ በሺዎች የሚቆጠር ዶላር እየተሸጠ ይገኛል፡፡ በአልቢኒዝም የተያዙና



በሰዎች እጆቻቸውና እግሮቻቸው የሚቆራረጡባቸው ተጠቂዎች እጅና እግሮቻቸው ከተቆራረጠ ብኃላ ባሉበት ጥለዋቸው ስለሚሄዱና የመጀመሪያ የጤና እርዳታም ስለማያገኙ አብዛኛዎቹ ጥቃት ከተፈጸመባቸው በኃላ ይሞታሉ፡፡ በሕይወት የሚተርፉም ካሉ በአብዛኛው የህግ ድጋፍ ወይም የህግ እርዳት አይደረግላቸውም፡፡

በዚሁ ዘርፍ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባቀረቡት ሪፖርት መሰረትም እ.ኤ.አ ከ2015 ብቻ ጀምሮ በ25 የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ከ448 በላይ የሚሆን ጥቃት በእነዚህ ሰዎች ላይ ተፈጽሟል፡፡ አብዛኛዎቹ ጥቃቶች የሚፈጸሙት በገጠሪቱ አካባቢዎች ላይ በሚገኙ ሰዎች መሆኑንም በሪፖርት ተጠቅሷል፡፡

አልቢኒዝም ያለባቸው ሰዎች ከሚፈጸምባቸው ጥቃቶች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው የፖለቲካ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ የምረጡኝ ዘመቻ ወቅት ሲሆን ይህም



ተወዳዳሪዎች ምርጫውን ለማሸነፍ ኃይል እንዲያገኙ ጤናማ እንዲሆኑና ሀብትም ለማግኘት ጠንቋይን የሚጠቀሙ አንዳንድ ፖለቲከኞች በመኖራቸውና ይህም በማድረግ የሚፈልጉት እንደሚያገኙ ስለሚታመን ነው፡፡

አልቢኒዝም ያለባቸው ሰዎች በአብዛኛው ከሌሎቹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተገልለው በአንድ ማዕከል/ መጠለያ ጣቢያ እየኖሩ የሚገኙበት ሁኔታ ሲሆን ያለው በአንዳንድ ሀገራት ውስጥ ልጆቹ በሚኖሩባቸው ማዕከላት ለከፋ የጤና ችግር፣ አካላዊና ወሲባዊ ቅጣት እንዲሁም ከወላጆቻቸው ጋር የማይገናኙ በመሆኑ የእነዚህ ሰዎች ችግሮች ተደራራቢ እየሆነ ይገኛል፡፡

ምንጭ፡-https://thisisafrica.me/increase-in-ritual-killings-of-albinos/
-http://globaldisability.org/2016/07/07/european-parliment-resolution-7-july-2016-situation-persons-albinism-africa

# ተግባራን በፎቶ



የ2010 በጀተ ዓመት በጤናው ዘርፍ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ መዋቅሮች ዓመታዊ የምክክር ጉባኤ ሲደረግ




በጤና ሚኒስቴር የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ሰራተኞች በከፊል



በጤናው ዘርፍ የአካል ጉዳተኞች ማካተቻ ማኑዋልን አፈፃጸምና ይዘት አስመልክቶ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ የህዝብ ክንፎችና አጋር አካላት በተገኙበት የምክክር መድረክ ሲደረግ



ከዚህ በፊት መሰረታዊ የምልክት ቋንቋ ስልጠና ለወሰዱ የጤናው ዘርፍ ሰራተኞች የማነቃቂያ (ሪፍረሸር) ስልጠና ሲሰጥ



በ2011 በጀት አመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የፌደራል ሆስፒታሎችና ተጠሪ ተቋት የሴ/ህ/ወ/ጉ መዋቅሮች ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በተገኙበት ዕቅድ አፈፃጸም ላይ ውይይት ሲደረግ





በአለም አቀፍ ደረጃ ለ107ኛ ጊዜ በሀገራችን ለ42ኛ ጊዜ ባለፈው ዓመት የተከበረውና የሴቶች ቀን ክብረ በዓል ከፊል ገጽታው



ወሲባዊ ጥቃት መከላከልና ምላሽ አሰጣጥ የአሰልጣኞች ስልጠና ከተለያዩ ሆስፒታሎች ለውጣጡ የጤና ባለሙያዎች ሲሰጥ



ኢሲዲዲ በሚባል ሀገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት በኩል ለአካል ጉዳተኞች (ለእንቅስቃሴ አካል ጉዳትና መስማት ለተሳናቸው ታካሚዎች) ምቹ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ ማስተካከያ ስራ የተሰራለት በአጋሮ ከተማ የሚገኘውን የወልዳ ጤና ጣቢያ የመስክ ምልከታ ሲደረግ




*በጤናው ዘርፍ የሴ/ህ/ወ/ጉ/ መዋቅሮች የ2011 በጀት ዓመት የስድስት ወር ዕቅድ አፈፃፀም ውይይት መድረክ ላይ ከግምገማው ባሻገር ለመዋቅር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እንዲሁም ለተጋባዥ እንግዶች በተለያየ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ስልጠና ሲሰጥ*



*ከተለያዩ ክልሎችና ከተማ መስተዳሮች ለተውጣጡ የጤናው ዘርፍ ባለሙያዎች የስርዓተ ፆታና አካል ጉዳተኝነትን ማካተት ስልጠና ሲሰጥ*



የጤናው ዘርፍ ለሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች ትኩረት አድርጎ እያካተተ እንዲሰራ ለበርካታ አመታት ሲተጉ የነበሩት የቀድሞ የክፍላችን ዳይሬክተርና በአሁኑ ጊዜ በአሃሪ የጥናትና ምርምር ማዕከል የሰው ሃብት ልማት ዘርፍ ምክትል ጄኔራል ዳይሬክተር በመሆን የተሾሙት ወ/ሮ ያምሮት እንዱዓለምን በዚህ ዓመት በሹመት ከክፍላችን የተዘዋወሩ ቢሆንም ሁልጊዜም ከእኛ ጋር ያሉና በተለያየ መልክ ለክፍላችን ለሚያደርጉት ድጋፍና እገዛ ለማመስገን እንወዳለን!!!




የመጽሔት አጠቃላይ ዲዛይን ዝግጅት፡- በዘውዱ ጉሉማ